# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 183 መጋቢት 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# በመሠረተ ልማት ጉድለት

## የነዋሪዎችን ኑሮ ያከበዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች



**አዲሱ ገረመው**

ነዋሪው በራሱ ጥረት አንድ ቧንቧ ከግለሰብ በመጥለፍ ለ88 ቤቶች እንዲደርስ ጥረት አድርጓል። ከዚህች ቧንቧ ውሃ ለመቅዳት የጀሪካን ሰልፉ ረጅም ነው። ሰው ውሃውን ለማግኘት "ቀኑን ለሠራዊት ሌቱን ለአራዊት" የሚለውን ሀገርኛ ብሂል ጥሶ ሌሊት ስምንት ሰዓት ጀሪካን አሰልፎ ውሃ ይቀዳል። ምክንያቱም አንድ ጀሪካን ለመሙላት ቢያንስ 20 ደቂቃ መጠበቅ ይኖርበታል።

የሕንጻ መወጣጫ አሳንሰሩ አልተገጠመም። ደረጃዎቹም ቢሆኑ በአግባቡ የተሠሩ አይደሉም። ለሕጻናት አስጊ ናቸው። ኮንትራክተሩ መሠል ሥራዎችን ጨርሶ እንዲሠራ ቢጠይቁትም ገንዘብ አልተለቀቀልኝም ብሎ መልስ እንደሚሰጣቸው ነው የቦሌ ቡልቡላ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች የተናገሩት። ይህ ችግር የአንድ ወይም ሁለት ሳይት ችግር አይደለም። ኢፕድ ተዘዋውሮ የተመለከታቸው በርካታ የጋራ መኖሪያ ቤት ሳይቶችም በተመሳሳይ

በመሠረተ ልማት ጉድለት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ

# በኢፕድ

## ለ34 ዓመት ያገለገለው ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ሥርዓተ ቀብር ዛሬ ይፈጸማል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ መጋቢት 11 ቀን 1958 ዓ.ም. ከአባቱ ከአቶ ግደይ አምባዬ እና ከእናቱ ሐረጉ ኀይትዖም በሱዳን ሀገር ከሰላ ተወለደ።

ጋዜጠኛ እዮብ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በዚያው ሱዳን ከሰላ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከታተለ ሲሆን ከዚያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በቲዩኒያን ከሰላ ቦይስ ማርች ተከታትሏል፡፡

በኢፕድ ለ34 ዓመት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በክልሉ የበልግ ሥራዎችን

## ቀድመው ለጀመሩ አካባቢዎች የአፈር ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘር እየቀረበ ነው

**አምሳሉ ፈለቀ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ የበልግ ወቅት ሥራዎችን አስቀድመው ለጀመሩት አካባቢዎች የአፈር ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘር እየቀረበ መሆኑን የሲዳማ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

ለ2016/17 የምርት ዘመን ለክልሉ ከሚያስፈልገው የአፈር ማዳበሪያ እስካሁን 72 በመቶ የሚሆነው ተገዝቶ መቅረቡም ተገልጿል፡፡

የቢሮው ምክትልና የግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ቡርቃ ቡጡላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በተያዘው የምርት ዘመን 266 ሺህ 950 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

በዚህም በአጠቃላይ ኤን ፒ ኤስ 101 ሺህ ኩንታል፤ ኤን ፒ ኤስ ቦሮን 63 ሺህ 20 ኩንታል እንዲሁም ዩሪያ 102 ሺህ 620 ኩንታል ተገዝቶ ለአርሶ አደሮች እንዲሰራጭ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በምርት ዘመኑ የአፈር ማዳበሪያ እንደ ሀገርም በወቅቱ ተገዝቶ መቅረቡን ያወሱት ኃላፊው፤ በዚህም ከዕቅዱ እስካሁን ኤን ፒ ኤስ 85 ሺህ 656 ኩንታል፡ ኤን ፒ ኤስ ቦሮን፣ 39 ሺህ 743 ኩንታል ዩሪያ፣ 66 ሺህ 931

በክልሉ የበልግ ሥራዎችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ቡርቃ ቡጡላ











ደስታ ገነሜ (ዶ/ር)

# በክልሉ በ74

## ትምህርት ቤቶች 184 ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ተገንብቷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ በ74 ትምህርት ቤቶች 184 ተጨማሪ አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎች መገንባታቸውን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ገለጸ፡፡ 369 ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች እየተገነቡ መሆናቸውም ተገልጿል፡፡

የትምህርት ቢሮው ምክትል ኃላፊ እና የመማርና ማስተማር ምዘና ዘርፍ ኃላፊ ደስታ ገነሜ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በትምህርት ንቅናቄ ከ258 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት ተሰብስቧል፡፡

ከተሰበሰበው ሀብት 254 ሚሊዮኑ በገንዘብ የተገኘ ድጋፍ ሲሆን፤ 4 ነጥብ 2 ሚሊዮኑ የተሰላው የጉልበት ድጋፍ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ምክትል ኃላፊው እንደተናገሩት፤ በ74

በክልሉ በ74 ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል







ዜና

# ኢንስቲትዩቱ የጀመራቸው የሪፎርም ሥራዎች እውን ለማድረግ
## የቴክኖሎጂ ሽግግር ያስፈልጋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የጀመራቸውን የሪፎርም ሥራዎች ከግብ ለማድረስ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ተገለጸ።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የዲጂታል ሚዲያ ስቱዲዮና የአስተዳደር ሕንጻ እድሳት አጠናቆ አስመርቋል።



ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል



ብሩክ ከድር(ዶ/ር)

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል በዕለቱ እንደገለጹት፤ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የጀመራቸው የሪፎርም ሥራዎች ከግብ ለማድረስ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ወይዘሮ ሙፈሪሃት አክለውም፤ የሥራ አካባቢን ፅዱ፣ ምቹና ተመራጭ ማድረግ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ ነው ብለዋል።

የዲጂታል ሚዲያ ስቱዲዮው ዘመኑ የዋጀ የክህሎት ሥልጠና ለመስጠት እንዲሁም ተደራሽነት ለማሳደግ የሚያስችል ነው ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ በኢንስትዩቱ የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች ወደ መሬት ማውረድ የሚቻልበት እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በተሻሻለው ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት ዜጎች ዘመኑ የደረሰበት የክህሎት ሥልጠና እንዲይዙ ለማስቻል ከተጀመሩ በርካታ የለውጥ ሥራዎች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቁመዋል።

የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ በዘርፉ ያለው እጥረት ወደ መልካም እድል ለመቀየርና ሃብት ማመንጨት የሚያስችል መሆኑንም ነው ወይዘሮ ሙፈሪሃት የገለጹት።

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪሃት ገለጻ፤ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በተቋማቱ ላይ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ውጤታማና አምራች ኃይል ለማግኘት የሚያግዝ ነው። የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት የአሠልጣኝ መምህራን ሥልጠናን ጨምሮ የተለያየ የረጅምና የአጭር ጊዜ ሥልጠና በመስጠት ላይ እንደሚገኝና ይህ የዲጂታል ስቱዲዮ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል።

ወይዘሮ ሙፈሪሃት አክለውም፤ ከዚሁ ሥራ ጎን ለጎን ከሰባት እስከ ስምንት ሄክታር በሚሆን መሬት ላይ ትልቅ የክህሎት ማዕከል ለመገንባት ዲዛይን ተሠርቶ ተጠናቋል ያሉ ሲሆን፤ በዚህ ዓመት ግንባታ እንደሚጀመር ጠቁመዋል።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) በበኩላቸው የተጀመሩ የለውጥ ሥራዎች ተግባራዊ ለማድረግ መሠረተ ልማት ሟሟላት ወሳኝ ነው ብለዋል።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብቁ አመራርና አሠልጣኞችን እንዲሁም ሠልጣኞች ለማፍራት ሥራዎች በትኩረት እየሠራ ይገኛል ያሉት ዶክተር ብሩክ፤ ዲጂታል ስቱዲዮው የሥልጠና ሥርዓቱን ለማዘመን ከሚረዱ የሪፎርም ስራዎች መካከል አንዱ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ብሩክ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ብቁ አሠልጣኞች አመራሮችና ሠልጣኞች ማፍራት ለኢንስቲትዩቱ ከተሰጡት ግቦች መካከል አንዱ ነው። ኢንስቲትዩቱ ከዚህ በተጨማሪ የዘርፉ አቅም የሚያሳድጉና ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ሥራዎች ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

የዲጂታል ሚዲያ ስቱዲዮው መስፈርቱን ጠብቆ ሙሉ ግብዓት ያሟላና በዘርፉ ያሉ ዓለም አቀፍ ልምድና እውቀት ማግኘት የሚቻልበት ስለመሆኑ በመድረኩ ተገልጿል።



# የአየር ንብረት ለውጥ በከተሞች ላይ የሚያደርሰውን
## ጫና ለመቋቋም በትብብር መሥራት ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአየር ንብረት ለውጥ በከተሞች ላይ የሚያደርሰውን ጫና ለመቀነስ በትብብር መሥራት እንደሚገባ የሲ40 አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ጊፍቲ ናዲ ገለጹ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በ‹ሲ40 ኔትወርክ› ትብብር የተዘጋጀ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ትናንት በአዲስ አበባ ተጀምሯል፡፡

የሲ40 አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ጊፍቲ ናዲ በሥልጠናው መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ የአየር ንብረት ለውጥ በከተሞች ላይ የሚያደርሰው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ከተሞች መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመርና በትብብር በመሥራት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ በሁሉም ላይ የሚስተዋል መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ተከትሎ በሚያጋጥሙ ድርቅና ሌሎችም የተፈጥሮ አደጋዎች ብዙዎች ሰለባ እየሆኑ ነው ብለዋል፡፡

የሲ40 የከተሞች ጥምረትም በየሀገራቱ ከተሞች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያከናውኑትን ተግባራት ያግዛል፡፡

የሲ40 አካታች የአየር ንብረት ለውጥ ፕሮግራምም በከተሞች መካከል ያሉ አቅሞችንና መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋት የአየር ንብረት ለውጥ፣ የቆሻሻ አወጋገድና የአካባቢ ጥበቃ ላይ የከተማ ነዋሪዎችን ፈተና ለመቀነስ ይሠራል፡፡

እስካሁን በተሠሩ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መገኘታቸውን አመላክተው፤ በተለይ አዲስ አበባ የሠራቻቸው ሥራዎች ለሌሎችም የአፍሪካ ከተሞች ትልቅ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ መቲ ታምራት በበኩላቸው፤ አዲስ አበባ ከተማ በአረንጓዴ ልማትና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ያላትን አስተዋፅዖ ለመጨመርና የተከናወኑ ሥራዎችን ለሌሎች ከተሞች ለማስተዋወቅ ብሎም ለማጋራት ያለመ ነው፡፡

አዲስ አበባ ባለፉት ዓመታት በቢሊዮን የሚቆጠር ችግኝ በመትከል የደን ሽፋኑን ከ3 በመቶ ወደ 17 በመቶ ማሳደጓን አስታውሰው፤ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይም ከተማዋ ያከናወነቻቸው ትልልቅ ሥራዎች እንደተሞክሮ የሚወሰዱ ናቸው ብለዋል፡፡

በዚህም እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን ቀመር በ2022 የሲ40 ዓለም አቀፍ ሽልማት አሸናፊ ሆናለች፡፡

በመሆኑም አዲስ አበባ ከተማ በአካባቢ ጥበቃ፣ በአረንጓዴ ልማትና በቆሻሻ አወጋገድ ላይ ያላትን ልምድ ለማሳየት ከሚሰጠው ሥልጠና ባለፈ ተሳታፊዎች በከተማዋ በዘርፉ የተሠሩ ሥራዎችን እንደሚጎበኙ ጠቁመዋል፡፡

በመርሐግብሩ ላይ አቢጃን፣ ዳካር፣ ዳሬሰላምና ደርባንን ጨምሮ ከስምንት የአፍሪካ ከተሞች የመጡ እንግዶች እንደሚሳተፉ ተጠቁሟል፡፡

# ዲጂታል ኢትዮጵያ
## 2025ን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 እስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የዲጂታል ክህሎት እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ አብዮት ባዩ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 እስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ በሥራ ላይ ላሉ ወጣቶች፣ እንዲሁም ከሥራና ከትምህርት ውጭ ለሚገኙ ዜጎች የዲጂታል ክህሎት እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ነው።



አብዮት ባዩ (ዶ/ር)

የእስትራቴጂው አንዱ ተግባር የዲጂታል ሥነ ምሕዳርን መገንባት መሆኑን የጠቆሙት አማካሪው፣ ለዚህም ቁልፉ ጉዳይ ለዜጎች ሥልጠና በመስጠት "ቢዝነሶች" ወደሥራ እንዲገቡ የሕግና የቁጥጥር ሥርዓቶችን ማሻሻል መሆኑን ጠቅሰው በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ አብዮት (ዶ/ር) ገለጻ፤ በእስትራቴጂው የቴሌኮም መሠረተ ልማቶች መስፋፋትን ተከትሎ የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር፤ ሁለት የቴሌኮም ኦፕሬተሮች በሥራ ላይ መሆን፤ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ መስፋፋት እና ሌሎችም ውጤቶች ተገኝተዋል። እድገቱ በቂ ነው ባይባልም ከጅምሩ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ መጥቷል።

ከሦስት ዓመታት በፊት 17 ሚሊዮን ገደማ የነበረው የኢንተርኔትና የዳታ ተጠቃሚዎች ቁጥር ኢትዮ-ቴሌኮም ባከናወናቸው ተግባራት ከ36 ሚሊዮን በላይ መድረሱን አመላክተው፣ በመንግሥት ደረጃ የንግድ ፍቃድ ማውጣት፣ የግብር ክፍያና ከግዢ ጋር የተያያዙ በርካታ አገልግሎቶች ወደ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት እየገቡ መሆናቸውን አንስተዋል።

በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ከ26 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በትምህርት ላይ ይገኛሉ፤ በዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሀገራዊ የዲጂታል ክህሎት ማዕቀፍ በማዘጋጀት፣ በማዕቀፉ መሠረት በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የክህሎት ማስጨበጥ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል።

የዲጂታል ኢኮኖሚ ትርጉም ባለውና አካታች በሆነ መልኩ ኅብረተሰቡን ለመለወጥ የሚችለው እያንዳንዱ ዜጋ ከዲጂታል ትሩፋቱ ሲጠቀም ነው ያሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንጻር ሲታይ ተደራሽነት ያላገኘ ብዙ የኅብረተሰብ ክፍል እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

አማካሪው እንደገለጹት፤ በእስትራቴጂው ተግዳሮት እየሆነ ያለው የመሠረተ ልማቶች በሁሉም ቦታዎች አለመዳረስ፤ የዜጎች የዲጂታል እውቀት ማነስ እንዲሁም ከሥራና ከትምህርት ውጭ የሆነውን ወጣት ማግኘት ነው። ለዚህም ሚኒስቴሩ እስትራቴጂዎችን ቀርጾ ወደተግባር በመግባት ላይ ይገኛል። በቀጣይም አብዛኛውን ኅብረተሰብ ከዲጂታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

አክለውም፤ "ዲጂታላይዜሽን እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ጥቅም ብቻ ሳይሆን የጎንዮሽ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት ዕድልም አለ። በተለይም በሐሰተኛ መረጃ ስርጭት፣ የግለሰቦችን መብት የሚነኩ ነገሮችና ከደኅንነት ጋር በተያያዘ በርካታ ጉዳቶች ሊደርሱ ይችላሉ። የጎንዮሽ ጉዳቶቹን በዘላቂነት መፍታት የሚቻለው ኅብረተሰቡ ግንዛቤ ሲኖረው ነው" ብለዋል።

በተያያዥነትም የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ ወደሥራ እየገባ መሆኑን ጠቁመው፤ በኮምፒዩተር፣ በኦንላይን የሚደረግ ማጭበርበርና የተዛባ መረጃ ስርጭት ወንጀሎች የሚዳኙበት የሕግ ሥርዓት ያለ በመሆኑ ይህንን የማጠናከር ሥራ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

# የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለቀጣናው
## ሠላምና ዕድገት ወሳኝ መሆኑን የዘርፉ ምሁር አስታወቁ


ፎቶ በረሁን ታደሰ

የኔነሽ ተመስገን (ዶ/ር)

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-ለቀጣናው ሠላምና ለጋራ ዕድገት የኢትዮጵያ የምትከተለው ዲፕሎማሲ ወሳኝ በመሆኑ ይህንኑ አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ሲሉ በዲላ ዩኒቨርሲቲ የሠላምና ፀጥታ ትምህርት ክፍል መምህር የኔነሽ ተመስገን (ዶ/ር) ተናገሩ።

መምህርት የኔነሽ ተመስገን (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለሠላምና ለጋራ ዕድገት ቅድሚያ የሰጠ በመሆኑ ለቀጣናው ሠላም ወሳኝ ነው።

ኢትዮጵያ ባላት የዲፕሎማሲ ታሪክ ጦረኛ ሳትሆን ሠላማዊና በመቻቻል ላይ የተመሠረተ ዲፕሎማሲን የምታራምድ ናት ያሉት ዶክተር የኔነሽ፤ ኢትዮጵያ በዘመናት መካከል የነበሯት መሪዎችና ዲፕሎማቶች የቀጣናውን ዲፕሎማሲ በጥንቃቄ ይዘው መምራታቸውን ጠቁመዋል።

በዲፕሎማሲ ረገድ ሁለት አይነት ዲፕሎማሲ መኖሩን የገለጹት ዶክተር የኔነሽ፤ ይህም "ለስላሳ ዲፕሎማሲና" እና "ጠንካራ ዲፕሎማሲ" መሆናቸውን አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ በሃርድ ዲፕሎማሲው የዓድዋ ጦርነትን አሸንፋ አቅሟን አሳይታለች፤ በለስላሳ ዲፕሎማሲውም የአፍሪካ ሀገራትን አንድ እንዲሆኑና ኅብረት እንዲፈጥሩ ማድረጓን ገልጸዋል።

ሀገሪቱ የበለጠ በንግግርና በውይይት ላይ የተመሠረተ ዲፕሎማሲን ስትጠቀም መቆየቷን አስታውሰው፤ በዚህም የበለጠ ወጤታማ የምትሆንባቸውን መደላድሎች ማመቻቸቷን ተናግረዋል።

ሀገሪቱ የራሷን ዲፕሎማሲ በሠላማዊና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ከመያዝ አልፋ በሌሎች ጎረቤት ሀገራት አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የምታከናውነው የሠላም ጥረት የሚወደስ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር የኔነሽ ገለጻ፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከቀጣናው ሀገራት ጋር በጋራ ስለምትጠቀምባቸው ጉዳዮች ስምምነት መድረሷን የማይፈልጉ አካላት የሚያደርጉትን ጥረት ለማክሸፍ ጥረት ማድረግ ይገባል።

ከባሕር በር ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ጫናዎችም ኢትዮጵያ በቂ ዝግጅት አድርጋ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚነሱ ሀሳቦችን በማጤን ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ ማከናወን ይገባል ብለዋል።

በተጨማሪም አብዛኛው የሀገሪቱ ዜጋ ስለወደብ ያለውን ግንዛቤ በማስፋት የህዳሴ ግድቡን የእኔ ነው ብሎ እንደያዘው ጉዳዩን በእኔነት ስሜት እንዲይዘው ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

የባሕር በር አለመኖር በርካታ ነገሮች እንድታጣ አድርጓታል ያሉት መምህሯ፤ የሀገሪቱ የባሕር በር ማግኘት በጂኦ ፖለቲካ ተጠቃሚ እንድትሆንና በቀጣናው ጠንካራ ሀገር እንድትሆን ያስችላታል ሲሉ ገልጸዋል።

ዶክተር የኔነሽ አይይዘው እንደተናገሩት፤ ለረጅም ዓመታት ለሀገሪቱ ዲፕሎማሲ ዕድገት ትልቅ ዋጋ የከፈሉበትን አካሄድ ይበልጥ በማጤን ለበለጠ ውጤት መሥራት ከማንኛውም ዜጋ ይጠበቃል።

ከሀገር ውስጥ ሰላምና ዲፕሎማሲውን በማጠናከር በቀጣናው ያለውን ሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አካሄዶች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚገባም መምህርቷ ጠቁመዋል።

# ከአራት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ
## ለመውሰድ ተመዝግበዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከአራት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ለመውሰድ መመዝገባቸውን የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮዳሔ አርዓያሥላሴ ገለጹ።

አቶ ዮዳሔ አርዓያሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 2018 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ቢያንስ 70 ሚሊዮን ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ለመስጠት እየተሠራ ነው። እስካሁን ድረስ ከ4 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ለመውሰድ ተመዝግበዋል።

ብሔራዊ መታወቂያ በተቋማት መካከል መናበብን በመፍጠር አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ዜጎችን ተደራሽ ለማድረግ ባንኮችን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመተባበር በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች በሺዎች የሚቆጠሩ መመዝገቢያ ጣቢያዎች ላይ ምዝገባ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

ብሔራዊ መታወቂያ ከዜጎች ባለፈ ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችም ተመዝግበው መታወቂያውን ያገኛሉ ያሉት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ ይህም ሕገወጥነትን ከመከላከል ጀምሮ እነዚህ ሰዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

አንድ ስደተኛ ኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የተሰጡት መብቶች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ያ ግለሰብ ግን በትክክል ስደተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ካምፕ ውስጥ የሆነ ሀገር ዜጋ ነኝ ብሎ ከተመዘገበ በኋላ የሆነ ቦታ ሄዶ የቀበሌ መታወቂያ ሊወስድ ይችላል ብለዋል።


አቶ ዮዳሄ አርዓያሥላሴ

የዲጂታል መታወቂያ ከተመዘገበ ግን በተቋማት መካከል መናበብ እንዲፈጠር በማድረግ መሰል ችግሮችን እንደሚያስቀርም ጠቁመዋል።

ከዚህም በተጨማሪ አንድ ተቋም ከሌላው ተቋም እንዲናበቡ በማድረግ ኢኮኖሚው ላይም አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታል ያሉት አቶ ዮዳሔ፤ ብዙ ሀገራት ዲጂታል መታወቂያ ከሰጡ ቆይተዋል። ኢትዮጵያ ዘግየት ብላ ሥራውን ብትጀምርም ከሌሎች ልምድ እንድንወስድና ስህተቶችን እንድናርም ያስችለናል ብለዋል።

ያለንን የሰው ሀብት ማወቅ ለልማት ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ መንግሥት ለብሔራዊ መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት ትልቅ ትኩረት መስጠቱን አስታውሰው፤ ዜጎችም የጉዳዩን አስፈላጊነት ተረድተው በየአካባቢያቸው በሚገኙ ምዝገባ ቦታዎች ቀርበው ለብሔራዊ መታወቂያ መመዝገብ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ከኢፌዴሪ ስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት እንዲሁም ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች ዲጂታል መታወቂያ መስጠት መጀመሩ ይታወሳል።

# በአማራ ክልል
## የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና የተደራሽነት ችግር እንዳይከሰት በትኩረት እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡-በአማራ ክልል ለ2016/17 የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና የተደራሽነት ችግር እንዳይከሰት በትኩረት እየተሠራ ነው ሲል የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በምርት ዘመኑም ከስምንት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለማስገባት ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አጀበ ስንሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በ2014/15 የምርት ዘመን የተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና የተደራሽነት ችግር በ2016/17 የምርት ዘመን እንዳይደገም በትኩረት እየተሠራ ነው፤ በምርት ዘመኑም ስምንት ሚሊዮን 57 ሺህ 900 ኩንታል አፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ የግዥ ሥርዓት እየተከናወነ ነው፡፡

ክልሉ ከ2014/15 የምርት ዘመን ከተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና የተደራሽነት ችግር ትምህርት በመውሰድ በተያዘው የምርት ዘመን ችግር እንዳይደገም ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አጀበ ገለጻ፤ ለ2016/17 የምርት ዘመን ስምንት ሚሊዮን 57 ሺህ 900 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለክልሉ እንዲቀርብ የግዥ ውል ተወስዶ እየተሠራ ነው፤ ውል ተወስዶ ወደ ከክልሉ ለማስገባት እየተሠራ ካለው ስምንት ሚሊዮን 57 ሺህ 900 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ የሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የግዥ ሥርዓት ተጠናቋል፤ ከዚህም ውስጥ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆነው ወደ ክልሉ የማስገባት ሥራ ተከናውኗል፤ ቀሪውን ከጅቡቲ ወደብ የማጓጓዝ ሥራ እየተሠራ ነው፤ እስከ መጋቢት አስርም የሚገባ ይሆናል፡፡

በክልሉ ከባለፈው ኅዳር ወር ጀምሮ የአፈር ማዳበሪያ የማቅረብና ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ በተሠራውም ሥራ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የቀረበ ሲሆን ከቀረበው ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ውስጥ 500 ሺህ ኩንታል ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የ2014/15 የምርት ዘመን የተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት የግዥ ሥርዓቱን የማሻሻልና ቀድሞ ግዥ የመፈፀም ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

በክልሉ የአፈር ማዳበሪያ የአቅርቦት ችግር እንዳይከሰት ብቻ ሳይሆን ግብዓቱን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ የማድረግም ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራም ባለው ሥራም የአንድ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ከፍተኛ ዋጋ ሦስት ሺህ 200 መቶ ሲሆን ዝቅተኛው ሁለት ሺህ 900 ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ አጀበ አያይዘውም፤ በክልሉ በሦስት ዞኖች ማለትም በሰሜን ጎጃም፣ በደቡብና በማዕከላዊ ጎንደር በፀጥታ ችግር ምክንያት የአፈር ማዳበሪያ ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም ብለዋል፡፡

የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የአፈር ማዳበሪያ ተደራሽ ለማድረግ በቀጣይ ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመው፤ በነዚህ አካባቢዎች ቀድመው የሚዘሩ ሰብሎችን አርሶ አደሮች እንዲዘሩ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግም አብራርተዋል፡፡

# በክልሉ በ74...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትምህርት ቤቶች 184 የመማሪያ ክፍሎች ተጠናቀዋል። በ69 ትምህርት ቤቶች 178 ክፍሎች ከቅድመ መደበኛ እስከ አንደኛ ደረጃ ተገንብተዋል። በአምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰባት የመማሪያ ክፍሎች ተጠናቀዋል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት 25 በመቶ በክልሉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል መታቀዱን የገለጹት ዶክተር ደስታ፤ በዚህም በአንደኛ ደረጃ ለ158 ትምህርት ቤቶች ጥገና ተደርጓል። በሁለተኛ ደረጃ ለ18 ትምህርት ቤቶች ጥገና ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለጻ በክልሉ 2 ሺህ 72 የመማሪያ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን፤ 7 መቶ 72 ሺህ ተማሪዎች ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባለው የትምህርት ደረጃ በዘንድሮ ዓመት እየተማሩ ይገኛል።

ከመማሪያ ትምህርት ቤቶች ግንባታ በተጨማሪ ስምንት ቤተ-መጽሐፍት ተገንብተዋል። መምህራኑ ምቹ ማረፊያ ማግኘታቸው የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳለጠ ስለሚያደርግ 50 የመምህራን መኖሪያ ተገንብቷል ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር ደስታ እንደገለጹት፤ ለተማሪዎች ምቹ የሆኑ መፀዳጃ ቤቶችን ከማዘጋጀት አንጻርም 188 መፀዳጃ ቤቶች ተገንብተዋል።

በክልሉ በትምህርት ንቅናቄው 235 ሺህ የንቅናቄ መድረኮች ከክልል ደረጃ እስከ ትምህርት ቤት የተደረገ ሲሆን፤ ከ300 ሺህ በላይ ሰዎች ተሳትፈዋል ብለዋል።

በክልሉ 90 በመቶ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች መሆናቸውን የገለጹት ደስታ(ዶ/ር)፤ የትምህርት ንቅናቄው መጀመር የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ዕድል ፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል።

ቀደም ብለው የነበሩ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ምቹ አለመሆናቸውን በመግለጽ፤ ንቅናቄው ተጀምሮ የትምህርት ቤቶቹ ግንባታ እና እድሳት መጀመር ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ሚናው የጎላ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

# በኢፕድ ለ34 ዓመት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አዲስ አበባ ከመጣ በኋላም ከአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ በጆርናሊዝም እና ኮሙኒኬሽን በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ ሲሆን ከመጋቢት 15 ቀን 1982 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወቱ እስካለፈበት እስከ መጋቢት አንድ ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአልዓለም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለ34 ዓመታት በተለያዩ የሥራ መደቦች አገልግሏል።

ጋዜጠኛ እዮብ ሥራውን በ 1982 ዓ.ም. በአልዓለም ጋዜጣ አራሚነት በመጀመር፤ በአልዓለም ጋዜጣ በከፍተኛ ሪፖርተርነት፤ በሜክአፕ ኤዲተርነት፤ በከፍተኛ አዘጋጅነት፤ በምክትል ዋና አዘጋጅነት በመጨረሻም በዋና አዘጋጅነት በኃላፊነት ሠርቷል።

ጋዜጠኛ እዮብ ከወይዘሮ መሠረት ገብረ ማርያም ጋር ትዳር በመመሥረት ሁለት ልጆችንም አፍርቷል።

የጋዜጠኛ እዮብ ግደይ የቀብር ሥነሥርዓትም በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ አቡነ ሀብተማርያም ገዳም ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ይፈጸማል፡፡

# በመሠረተ ልማት ጉድለት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ችግር ውስጥ ይገኛሉ።

አቶ አበበ ባይነሳኝ በቦሌ ቡልቡላ ኮንዶሚኒየም የብሎክ 29፣ 30፣ 31 እና 32 ብሎክ አስተዳደር ሲሆኑ፤ ቤቶቹ የቆዩና በቅርብ ጊዜ የተሠሩ መሆናቸውን ያነሳሉ። ቆየት ያሉት ውሃ ሲኖራቸው መብራት ግን የላቸውም። አንዱ ብሎክ ግን ውሃም መብራትም እንደሌለው ይገልጻሉ። ወደ 180 ቤቶች የሚሆኑት ውሃ የሚያገኙት ከሌላ ቦታ በመጥለፍ እንደሆነም ይናገራሉ። "የሚመለከታቸውን አካላት ውሃና መብራት ስንጠይቅ መብራት ካልገባላችሁ ውሃ ማስገባት አንችልም ይሉናል። ይህንን ተመላልሰን ጠይቀን ምላሽ ባለማግኘታችን ተስፋ ቆርጠን ትተናል። የዚህ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪ ከፍተኛ ለሆነ ምሬትና ብሶት ተጋልጧል" ይላሉ።

አቶ አበበ፤ "ቤቶች ስንሄድ መብራት ኃይል ሂዱ ይላሉ። መብራት ኃይል ስንደውል ደግሞ ብር አልተከፈለም ብለው ያጉላሉናል። በአሁን ወቅት መብራት ለማሰራጨት ቆጣሪ ተገጥሟል። ይህ አገልግሎት ሳይሰጥ ሦስት ወር አልፎታል። የጣሪያ ግድግዳ ግብር በመክፈል ግዴታችንን እየተወጣን ቢሆንም መብታችን የሚያስከብርልንን አጥተናል" ሲሉ ነው ቅሬታቸውን በምሬት የሚገልጹት።

መሠረተ ልማቱ ባለመሟላቱ ምክንያት ከ80 በላይ የጂ7 ቤቶች ውስጥ ወደ ቤታቸው የገቡት 30 ሰዎች ብቻ መሆናቸውን የሚጠቅሱት አቶ አበበ፤ የገቡትም መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው ሳይሆን የቤት ኪራይ የመክፈል አቅም ስለሌላቸው ከዚህ ችግር ለማምለጥ ሲሉ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ከደህና ቤታችን ለልማት በሚል ተነስተን መጥተን አሁን ላይ የውሃ ጥምና የመብራት ችግር እያሰቃየን ነው በማለት፤ የችግሩን አሳሳቢነት ለመግለጽ ብዙ ቦታ መሄዳቸውንና ምንም መፍትሔ ማግኘት አለመቻላቸውን ለኢፕድ አብራርተዋል።

ባለሰባት ወለሉ ሕንጻ ሊፍት እንዳልተገጠመለትና ልጆች ጉድጓድ ውስጥ እንዳይገቡ በሚል ኅብረተሰቡ በቆርቆሮ እንደሸፈነውም የሚገልጹት አቶ አበበ፤ ይህ ግን ዘላቂ መፍትሔ ካላገኘ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችልም ተናግረዋል።

አቶ አበበ እንደሚሉት፤ ባዶ ቤቶችን ማንም ሰው እንዳሻው እየተጫወተባቸው ነው። ቤት እየሰበሩ የሚገቡ አሉ። አንዳንዶቹን ቤቶችም ወደ መፀዳጃ ቤትነት የቀየሩ አሉ። በሚመለከተው የመንግሥት አካላት ቁጥጥር እየተደረገበት አይደለም።

ወይዘሮ ማርታ ሽመልስ ቦሌ ቡልቡላ ብሎክ 31 ነዋሪ ሲሆኑ፤ ወደ ቤታቸው ከገቡ ሦስት ዓመታትን አስቆጥረዋል። ሆኖም መብራትና ውሃ መሠረታዊ ችግር መሆኑን ይናገራሉ። እርሳቸው ያሉበት ብሎክ ውሃ በሳምንት ጥቂት ቀናት ብቻ በተቆራረጠ መንገድ ቢመጣላቸውም፤ መብራት ግን እስካሁን እንደሌለ ነው የሚገልጹት። ግቢው ጭምር ለኑሮ ምቹ ሆኖ ባለመሠራቱ በራሳቸው ወጪ እያሠሩ እንዳለም ጠቅሰዋል።

ግብር በመክፈል ግዴታችንን እየተወጣን ቢሆንም ውሃና መብራት የማግኘት መብታችን ተነፍገናል የሚሉት ወይዘሮ ማርታ፤ "መሐል ከተማ ሊባል በሚችል ቦታ ላይ ተቀምጠን መብራት ማጣታችን ተገቢ አይደለም። ይህም ሕዝብን በእጅጉ እያማረረ ነው" ሲሉ ይገልጻሉ።

በብሎክ 32 የጂ7 ሕንጻ ላይ መጀመሪያ ብቻቸውን እንደገቡ የሚጠቅሱት ወይዘሮ አበባ ግርማይ በበኩላቸው፤ የጋራ መኖሪያ ቤቱ ውሃ ስለሌለው ላለፉት ሁለት ዓመታት ሙሉ በደካማ አቅማቸው በጀሪካን እየተሸከሙ ገንዘባቸውንም ጉልበታቸውንም እያባከኑ ስለመሆናቸው ይናገራሉ። መብራት ከግለሰብ ቀጥለው እየተጠቀሙ እንደሆነም ገልጸዋል። አንድ ጀሪካን ውሃ እስከ 30 ብር በመግዛት፣ ለተሸካሚ የሚከፈለውን ጨምሮ በቀን ብዙ ገንዘብ እያወጡ እንዳለም ጠቅሰዋል።

ይህንን ችግር ሲያመለክቱ ከእሺታ ውጪ ገቢራዊ የሆነ ተጨባጭ መልስ ማግኘት ባለመቻላቸው ተስፋ ቆርጠው በችግር ውስጥ ሆነው እየኖሩ መሆናቸውንም ገልጸውልናል።

ልጅ ይዞ ልብስ ማጠብ፣ ፅዳት መጠበቅ አለ። ይህ ኮንዶሚኒየም ነዋሪ ለሆነ ደግሞ ችግሩ ይብሳል። ለዚህ ነው ኑሮው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሆነባቸው። "በመንግሥት በኩል የሚወርዱ ማናቸውንም ትዕዛዞች እያከበርን ግብርም እየከፈልን ነው። የኛ መብት ግን አልተጠበቀልንም፤ የሚመለከተው አካል ይህንን ችግር በአፋጣኝ እንዲፈታለን እንፈልጋለን" ሲሉ ጠይቀዋል።

ሕይወት ተሾመ በቦሌ በሻሌ ሳይት የጋራ መኖሪያ ብሎክ 37 ነዋሪ ናቸው። ዕጣው የወጣላቸው በ2011 ዓ.ም ሲሆን እስካሁን በሳይቱ የመብራትና ውሃ እንዲሁም የአሳንሰር መሠረተ ልማት እንዳልተሟላ ይገልጻሉ።

የሦስት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ሕይወት፤ የጋራ መኖሪያ ቤቱ ውሃ ስለሌለው ሕጻናቱን መፀዳጃ ለማስጠቀም ሁልጊዜ ከሦስተኛ ወለል ላይ ወደ ታች መውረድ የግድ እንደሚላቸው ይናገራሉ። ውሃ የሚጠቀሙት በጋሪ ከሚያዞሩት ሰዎች ላይ በመግዛት ሲሆን ለአንድ ጀሪካን 25 ብር እየገዙ ለተሸካሚው ደግሞ ተጨማሪ ክፍያ እንደሚፈጽሙ ነው የሚገልጹት። ይህም ለአንድ ጀሪካን ውሃ 50 ብር ድረስ ወጪ ያስወጣል ነው ያሉት። ብዙ ልጅ ያለው ቤተሰብ 10 ጀሪካን ቢጠቀም በቀን እስከ 600 ያህል ብር ወጪ ሊያወጣ እንደሚችልም ነው የሚጠቅሱት፤ ይህ ደግሞ ተከራይቶ ከመኖር የሚተናነስ አይደለም ነው ያሉት።

በዚህ ሳይት መብራት ለነዋሪው ስላልገባ ሳይቱን ሲሠራ ከቆየው ኮንትራክተር የኤሌክትሪክ ኃይል የጠለፉ ብሎኮች እንዳሉና ለዚህም አንድ ቤተሰብ በወር 800 ብር እንደሚከፍል ገልጸዋል።

እርሳቸው ባሉበት ብሎክ ላይ ከ100 በላይ ቤቶች ቢኖሩም እስካሁን የገቡት ግን ስምንት ብቻ ናቸው። አብዛኞቹ ያልገቡት መሠረተ ልማቱ ባለመሟላቱ ምክንያት እንደሆነ ገልጸዋል። ቤቶቹ የንግድ ቤቶች ታሳቢ ተደርገው የተሠሩ ቢሆንም ሥራ ባለመጀመራቸው ሱቆችን በቅርብ ርቀት በበቂ ሁኔታ አለማግኘትም አንዱ ችግር ነው ብለዋል። የሚመለከተው አካል የገባውን ውል ፈጽሞ የነዋሪውን ኑሮ ለማስተካከል ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

በዚህ ሳይት፤ ታማሚዎች ሕንጻው ላይ በደረጃ መመላለስ ስለማይችሉ ምግብና መሰል ግብዓቶች ከታችኛው ወለል ላይ ካለው ሱቅ በገመድ እየተጎተተ እንደሚደርስላቸው የኢፕድ ሪፖርተሮች መመልከት ችለዋል።

አብርሐም ለላንጎ ቦሌ በሻሌ ሳይት የጋራ መኖሪያ ብሎክ 28 ነዋሪ ሲሆን፤ የ2011 የሁለተኛው ዙር 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ዕድለኛ ነው። የጊቢው ኮሚቴ አስተባባሪም ነው። በቦሌ በሻሌ ሳይት 58 ያህል ብሎኮች ያሉ ሲሆን፤ 40/60 ከያዛቸው ሳይቶች ትልቁ እንደሆነም ጠቅሷል።

እንደ ነዋሪው ገለጻ፤ በ2011 የወጡት 31 ብሎኮች ናቸው። ቀሪ 27 ብሎኮች በ2015 የወጡ ናቸው። ባለ 9፣ ባለ13 እና ባለ 15 ወለል ያላቸው ናቸው። ወደ ኋላ የቀረ ሳይት ነው። ዕጣው ላይ ለመድረስ ባለው ጊዜ አምስት ዓመት ያህል ወስዷል። ዕጣው ከወጣ በኋላም ሰው መግባት የጀመረው ከአምስት ዓመት በኋላ ነው።

በሳይቱ የፍሳሽ ሥራው ባለፈው ሁለት ወር ገደማ መጠናቀቁን በመጥቀስ፤ መብራትና ውሃውም በተመሳሳይ ቢገቡና ችግሩ ቢፈታ በመሠረተ ልማት አለመሟላት ምክንያት ወደ ቤቱ ያልገባው ነዋሪ ወደ ቤቱ እንደሚገባ ይጠቅሳል። ይህም ከተማ ውስጥ ያለውን የቤት ችግር ይቀንሳል ይላል።

በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የቅርንጫፍ ሦስት ሥራ አስኪያጅ አቶ አየነው ዓለሙ፤ በቦሌ በሻሌ 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች 6 ሺህ 509 ቤቶች መኖራቸውን፤ ከዚህ ውስጥ 5 ሺህ 374 የመኖሪያ እንዲሁም 1 ሺህ 135 የንግድ ቤቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዕጣው የወጣው በ2011 እና 2015 ዓ.ም በሁለት ዙር እንደሆነ በመጥቀስ፤ እስካሁን የገቡት እስከ ሁለት መቶ የሚደርሱ ናቸው ብለዋል። አብዛኛው ሰው በመሠረተ ልማት አለመሟላት ምክንያት እንደሚቸገርና የመሠረተ ልማት ተቋማት የግብዓት አቅርቦትን ጨምሮ የተለያየ ምክንያት ሊኖራቸው እንደሚችሉ ተናግረዋል። የመብራትና የውሃውን የሲቪል ሥራ የሚያከናውነው የመንገዶች ባለሥልጣን እንደሆነና ይህ እየተጠናቀቀ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ቤቶች ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ስጦታው አካለ፤ ነዋሪዎች ዕጣ ካወጡባቸው ጊዜያት ጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ቤታቸው እንዲገቡ በከተማ አስተዳደሩ በኩል ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም፤ አሁንም ድረስ ያልገቡ እንዳሉ ገልጸዋል። ለመኖር የሚያስችሉ ዋና ዋና መሠረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት ስላለባቸው ይህን በመጠበቅ ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል።

በ2015 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ 30 ባለው ብቻ እስከ 130 ሺህ የሚሆን ሕዝብ ወደ ቤቱ ማስገባት ተችሏል። ከ2015 በጀት ዓመት ያደሩ ሥራዎች ከአቅም በላይ ሆነው የተላለፉ ናቸው። ሆኖም እስካሁን ዕጣ ከወጣላቸው 139 ሺህ ነዋሪዎች ውስጥ ወደ 7 ሺህ ገደማው ወደ ቤታቸው አልገቡም።

"እነዚህን ቤቶች በ2016 እቅዳችን አድርገን እስካሁን ሰዓት ድረስ እየሠራን እንገኛለን። ስለዚህ ችግሩ እንዳለ እናምናለን። ነገር ግን ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው" ብለዋል።

ከምክንያቶቹ አንዱና ዋነኛው የፋይናንስ ችግር እንደሆነም ኢንጂነር ስጦታው ገልጸዋል። የኅብረተሰቡ ቁጠባ ሙሉ ቤቱን ስለማይሠራ ዛሬ ላይ ኮንስትራክሽን በምን ያህል ብር እንደሚገነባ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከመንግሥት ወይም በባንክ ብድር ተበድረን ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ እዳ ውስጥ ገብተን ነው ቤት እየገነባን ያለነው ያሉት ኢንጂነር ስጦታው፤ አሁን ካለው የኮንስትራክሽን ዋጋ አንጻር ኅብረተሰቡ ምንም እንኳን የሚጠበቅበትን መቆጠብ ቢችልም በእጅጉ እንደሚያንስ አስታውቀዋል። በቂ ባለመሆኑ ምክንያት የፋይናንስ እጥረት መግጠሙንና እጥረቱን ለመሙላት የፋይናንስ ምንጭ እየተፈለገ መሠረተ ልማት እንዲሟላና ቤቶቹ ምቹ እንዲሆኑ የቀሩት ቤቶች እንዲጠናቀቁ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል። ችግር ያለባቸው ቤቶችን በየሳይቱ ምን እንደጎደላቸው ተለይተው ችግሩን ለመፍታት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ሌላው ችግር የተቋራጮች አቅም ውስንነት መሆኑን የገለጹት ኢንጂነር ስጦታው፤ "በጦርነት ውስጥ የቆየን ስለሆነ ተቋራጮች በቂ ሥራ እየሠሩ ስላልሆነ ለሠሩት ሥራ ጭምር የፋይናንስ ጥያቄ ሲጠይቁ ምላሽ መስጠት ባለመቻላችን ምክንያት በሙሉ አቅማቸው ሥራ እየሠሩ አይደለም" ብለዋል። የፋይናንስ እጥረቱ በተቋራጮች አቅም ላይ ጫና መፍጠሩንም ነው የጠቀሱት።

በኅብረተሰብ ተሳትፎ የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉና ሁሉም ሥራ በመንግሥት የሚሠራና የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ኅብረተሰቡ ራሱ ቤቱ ከተሠራለት ገብቶ ማልማት በጋራና በትብብር መሥራትን እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

እንደ ኢንጂነር ስጦታው ገለጻ፤ የቦሌ በሻሌ ሳይት የጎደሉት ነገሮች አሉት። ከእነዚህም መካከል አንዱ ሊፍት ሲሆን በቀጣይ የሚስተካከል ይሆናል። አሁን ካለው የዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ ትልቅ በጀት የሚጠይቅ ነው። ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ጊዜ ወስዷል። ነገር ግን አሁን ላይ አቅራቢዎቹ ውል ገብተው ባስቸኳይ ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ ስለሆነ በቀጣይ አንድ ወይም ሁለት ወር ውስጥ የሊፍት ገጠማ ሥራ ይከናወናል። ከውሃ ችግር ጋር ተያይዞም ፓምፕ ጨረታ ላይ ስለሆነ በጥቂት ወራት እንደሚገጠም ጠቅሰዋል።

# በክልሉ የበልግ ሥራዎችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኩንታል በአጠቃላይ 192 ሺህ 329 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶ ወደ ግብዓት ማከማቻ ማዕከል መቅረቡን ተናግረዋል። ይህም ከዕቅዱ 72 በመቶ መከናወኑን ነው የጠቆሙት፡፡

በዚህም የበልግ ወቅት ሥራዎችን ቀድመው ወደ ጀመሩት በቆላማው በቆሎ እና ቦሎቄ እንዲሁም በደጋማው ድንች ለሚያለሙ አርሶ አደሮች ቅድሚያ ተሰጥቶ በአሁኑ ወቅትም በወረዳዎችና ቀበሌዎች በሚገኙ ማኅበራት በኩል ኤን ፒ ኤስ እና ኤን ፒ ኤስ ቦሮን 48 ሺህ ኩንታል የቀረበ ሲሆን፤ ዩሪያ ዘግይቶ ቢደርስም 15 ሺህ ኩንታል በላይ እንዲሰራጭ ተደርጓልም ብለዋል።

ይህም ዘንድሮ ተገዝቶ ከቀረበው የተሰራጨ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት ከቀረበው ውስጥ በወረዳዎች የግብዓት ማከማቻ መጋዘኖች ከመስኖ ልማት ወደ በልግ የተላለፈው ኤን ፒ ኤስ እና ዩሪያ 25 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ እንደሚገኝም ኃላፊው ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት የበልግ ሥራን አስቀድመው ወደ ጀመሩት አካባቢዎች አስፈላጊው ግብዓት ያለምንም እጥረት እየቀረበ መሆኑን አስረድተዋል።

ይሁን እንጂ ባለፈው ዓመት በበልግ ወቅት እንደ ሀገር የገጠመውን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እጥረትን ተከትሎ በክልሉ በሦስት ወረዳዎችም የግብዓት ብክነት መከሰቱን የጠቆሙት አቶ ቡርቃ፤ በዚህ ድርጊት የተሳተፉ ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን ይናገራሉ።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፡- ከዚህ ቀደም ይከሰት የነበረውን የአፈር ማዳበሪያ ስርቆትና ብክነትን ለመቅረፍም አርሶ አደሮቹ በባንክና በሌሎችም ዘመናዊ የክፍያ ዘዴዎች ቀድመው በመክፈል መሬታቸውን አርሰው ያዘጋጁት አርሶ አደሮች የሌላ ወገን ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ግብዓቱን በቀጥታ መውሰድ የሚችሉበት አሠራር ተመቻችቷልም ነው የተባለው። ይህም አላስፈላጊ የሆነ የነጋዴዎችና ደላሎች ጣልቃ ገብነትን እየቀረፈ እንደሆነም ተጠቁሟል።

አምና በተመሳሳይ ወቅት በግብዓት አቅርቦት በኩል የገጠሙ ውስንነቶችን በመቅረፍም ባለፈው የመኸር እና የመስኖ ልማት ሥራ ወቅት አስፈላጊው ግብዓት ለአርሶ አደሮቹ እንዲሰራጭ መደረጉን አክለዋል።

የምርጥ ዘር አቅርቦትን በተመለከተም እንደ ክልል ለበልግ ወቅት 15 ሺህ ኩንታል የተለያየ የበቆሎ ምርጥ ዘር እንደሚያስፈልግና ከዚህ ውስጥም እስካሁን 9 ሺህ ኩንታል በላይ መቅረቡን የተናገሩት ኃላፊው፤ ይሁን እንጂ ምርጥ ዘር ከሚያባዙ ሌሎች ክልሎች የሚገኝ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በፀጥታ ችግር ምክንያት አስፈላጊው ምርጥ ዘር በበቂ ሁኔታ አለመቅረቡን አንስተዋል።

ይህንን ችግር ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመቅረፍና የምርጥ ዘር ፍላጎትን በክልሉ ለማሟላትም በአሁኑ ወቅት 400 ሄክታር መሬት በመለየት ታርሶ ለምርጥ ዘር ማባዣነት እንዲውል ለማድረግ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ቡርቃ፤ ከዚህ ውስጥም አብዛኛው መሬት መታረሱንና 150 ሄክታር መሬት አርሶ የማዘጋጀት ሥራ ብቻ እንደሚቀር ጠቁመው፤ በቀጣይ በክልሉ የምርጥ ዘር እጥረት እንዳይከሰት ለማድረግ ዕቅድ መያዙንም ተናግረዋል።

አያይዘውም አርሶ አደሮቹ ትክክለኛ ግብዓት አስመስለው ገበያ ላይ በሚያቀርቡ ደላሎችና ነጋዴዎች ሳይታለሉ በመንግሥት በኩል የሚቀርበውን ግብዓት ብቻ ተጠቅመው እንዲያለሙና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በትራፊክ አደጋ መሞት ይብቃ!

ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ተግባርና እንቅስቃሴ የማቅለሉን ያህል፤ ፋይዳውን በልኩ ተገንዝቦ ከመጠቀም አኳያ የሚታዩ የእውቀት፣ የክሂሎት፣ የሥነምግባርና ተያያዥ ችግሮች ምክንያት በሰው ልጆች ሕይወት ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖና ጉዳትም ቀላል አይደለም።

በዚህ ረገድ የተሽከርካሪ (መኪና) በሰው ልጆች የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ከማቅለል አኳያ ከፍ ያለ ሚናን እየተወጣ ይገኛል። በዚህም ሰዎች መድረስ የሚፈልጉበት ቦታ በፍጥነትና በምቾት እንዲደርሱ፤ ደኅንነታቸውና ንብረቶቻቸው ተጠብቆ ከቦታ ቦታ በቀላልና በቀለጠፈ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ፤ የሰው ልጆች እንቅስቃሴን የተሳለጠ አድርጓል።

ይሁን እንጂ ይሄንን የሰው ልጆች ኑሮ አቅላይ ተሽከርካሪ/መኪና፤ በእውቀት፣ በአቅም፣ በክሂሎት፣ በሕግና ሥርዓት እንዲሁም ሥነምግባርን ተላብሶ ካለመጠቀም አኳያ እያደረሰ ያለው ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ በትራፊክ አደጋ ምክንያት ዓለማችን ሚሊዮኖችን በየዓመቱ ታጣለች። ኢትዮጵያም በየዓመቱ የሺዎችን ሕይወት ትነጠቃለች፤ በቢሊዮን የሚገመት ንብረትም ታጣለች። ለምሳሌ፣ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ አንድ ሺህ 358 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን አጥተዋል። ሁለት ሺህ 672 ሰዎች ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

የመኪና አደጋ በሰው ሕይወት ላይ ብቻ ሳይሆን በንብረት ላይም ከፍ ያለ ዋጋን እያስከፈለ ያለ የሀገር ኢኮኖሚ አውዳሚ መሆኑ አልቀረም። በሀገራችን ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ብቻ በትራፊክ አደጋ ምክንያት ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ንብረት ወድሟል። በዚህ ረገድ የተጠቀሰው ቁጥር ከአምናው አንጻር ሲታይ መቀነስ የታየበት ቢመስልም፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየታየ ያለው አሰቃቂ የመኪና አደጋ ግን ችግሩ አሁንም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለመሆኑ አመላካች ነው።

በዚህ መልኩ አሳሳቢ ሆኖ ለሚታየው የትራፊክ አደጋ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላል። ለምሳሌ የአሽከርካሪዎች ቸልተኝነት፣ ሥነምግባር እና እውቀት ዋነኛው ጉዳይ ተደርጎ በተለያየ መልኩ ይገለጻል። ይሄ ደግሞ ከአሽከርካሪዎች የአሽከርካሪነት ፍቃድ (መንጃ ፈቃድ) አሰጣጥ ጋር አብሮ የሚቆራኝ ነው።

ምክንያቱም አንድ አሽከርካሪ የአሽከርካሪነት ፈቃድ ሲወስድ፤ ለወሰደው ደረጃ የሚመጥን የዕውቀት፣ የንቃትና ሥነምግባር አቅምን ጨብጧል ተብሎ ነው። ይሁን እንጂ በእኛ ሀገር ሁኔታ በአመዣኙ የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ በእጅጉ ለሙስና የተጋለጠ፤ አንዳንዴም "ከከፈሉ ቤት ድረስ ይሄዳል" የሚል ቅሬታ ጭምር የሚቀርብበት ነው።

ሌላኛው ምክንያት ተደርጎ የሚነሳው፣ የእግረኞች ያልተገባ የመንገድ አጠቃቀም፣ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት መጓደልና የመንገድ ሁኔታ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ የሚነሱ ችግሮችም አንድም ከግንዛቤ ችግር፤ ካልሆነም ከቸልተኝነትና ሥነምግባር ጉድለት ጋር የሚተሳሰሩ ናቸው። ለምሳሌ፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ችግር፤ ከዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ፍተሻ እና ቦሎ አሰጣጥ ችግር ተነጥሎ የሚጠቀስ አይደለም።

የመንገድ ሁኔታም፣ መንገዶች ሲሠሩ መንገድ የሚፈልገውን ደረጃ እና ምልክቶች አሟልቶ ካለመሥራት ጋር የሚገናኙ ናቸው። እናም የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ችግርም ሆኑ የመንገድ ሁኔታ በየዘርፉ ከተሠማሩ ተቋማትና ግለሰቦች የአቅም አልያም የሥነምግባር መጓደል ጋር ተገናዝበው የሚነሱ ናቸው።

ምክንያቱም አቅም ያለው እና መልካም ሥነምግባርን የተላበሰ ተቋምና ግለሰብ፤ የቴክኒክ ችግር ያለበትን ተሽከርካሪ ብቃት አለው ብሎ ቦሎ አይለጥፍለትም። በተመሳሳይ ለትራፊክ እንቅስቃሴ ምቹ ያልሆነ መንገድ ገንብቶም ለተሽከርካሪ ክፍት አያደርግም።

እዚህ ላይ ሊታሰብ የሚገባው ጉዳይ ችግሩ ምንም ይሁን፣ በማንም ምክንያት ይፈጠር፤ እየሆነ ያለው ጉዳይ በዜጎች ሕይወትና አካል ላይ፣ በሀገር ኢኮኖሚም ላይ እየፈጠረ ያለው ቀውስ በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑን መገንዘብ እና ችግሩን ለመሻገር የሚያስችሉ ርምጃዎች መውሰድ ላይ ማተኩር የሚገባ መሆኑን ነው።

ለዚህ ደግሞ ከመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ነቅሶ ማረምና ርምጃ መውሰድ፤ ከትራፊክ ተቆጣጣሪ አካላት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ተከታትሎ ማረምና ማነጽ፤ ከተሽከርካሪ የቴክኒክ ችግር ጋር የሚታየውን ጉድለትም በወጉ ፈትሾ ችግሩን ከምንጩ ለመግታት መጣር፤ ከመንገድ ሁኔታ ጋር ያሉ ጉድለቶችንም ተመልክቶ ማረም፤ የግንዛቤ ክፍተቱንም መሙላት ተገቢ ነው።

ይሄን ማድረግ ደግሞ የዜጎችን (የእናቶችን፣ የሕጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋውያንን) ሕይወትም አካልም መታደግና የሀገር ኢኮኖሚንም መጠበቅ ነው። ለዚህ ደግሞ አይመለከተኝም የሚል አካል ሊኖር አይገባም። አሽከርካሪዎች፣ የትራፊክን ተቆጣጣሪዎች፣ መንገድ ገንቢዎች፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት አረጋጋጮች፣ እግረኞች፣... ሁሉም በኃላፊነት ስሜት ሊሠሩ ይገባል።

ይሄን ማድረግ ሲቻል የትራፊክ አደጋን መቀነስ፤ መኪናን የሰው ልጅ ሕይወት አቅላይ ማድረግ፤ በመኪና አደጋ ምክንያት የሚቀጠፈውን የሰው ሕይወት፤ የሚጎድለውን አካል፤ እና የሚወድመውን ንብረት ማዳን እንችላለን። በመሆኑም የትራፊክ/የመኪና አደጋ አሁን ላይ እያደረሰ ካለው ከፍ ያለ ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት አንጻር አሳሳቢነቱን በመረዳት ተገቢውን እርምትና ርምጃ መውሰድም ዘርፉን ከሚመሩ ተቋማት ይጠበቃል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የተፋሰስ ልማት-ለምርታማነት

ግርማ ሞገስ

የተፋሰስ ሥራ ከማኅበረሰብ አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎች አንዱ ሲሆን፤ በግብርና ምርት ሥርዓቶች ላይ ለሚተገበሩ የሥነ ምሕዳር ሂደቶች ውጤታማነት የሚኖረው አስተዋፅዖ የጎላ ነው። በኢትዮጵያ ከ1970ዎቹ አንስቶ የተፋሰስ ልማት ወይም የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች በስፋት በዘመቻ መልኩ ሲሠሩ ቢቆዩም፤ በተጠቃሚው እና አስፈጻሚው አካል ያለው መናበብ የላላ በመሆኑ የተደከመበትን ያህል ውጤታማ እንዳልነበር በዘርፉ የተጻፉ መዛግብት ያስረዳሉ።

በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍም የግብርና ሚኒስቴር ከክልሎች የግብርና ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የማልማት ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎቸው እንደሚጠቁሙትም ማኅበረሰቡን በባለቤትነት ባሳተፈ መልኩ በተለያዩ ክልሎች ንዑስ ተፋሰሶችን ተግባራዊ ተደርጎ ውጤታማ መሆን ተችሏል። ለምሳሌ፣ የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ወዲህ ለተፋሰስ ልማት ሥራዎች በተሰጠው ትኩረት ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የዓባይ ምንጭን ጨምሮ ገባር ወንዞች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ የማልማት ሥራ ተሠርቷል። በዚህ መልኩ የተከናወነው ሥራም የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ አድርጓል።

ይሁን እንጂ አብዛኛው ኢትዮጵያ ክፍል ደጋማ በመሆኑ ዛሬም ድረስ ለአፈር መከላት የተጋለጠ ነው። ከዚህ አኳያ ቀጣይ የተፋሰስ ልማት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ኅብረተሰቡን በተለይም አርሶ አደሩን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎችን ጥቅም እንዲረዳ በማድረግ ልማቱን በባለቤትነት እንዲያከናውን ማድረግ ያስፈልጋል። የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ሲሠሩና ሲጠናከሩ ደኖች ያገግማሉ፣ የተራቆቱና እና የተጎራረዱ የወል መሬቶች ከመጠገናቸውም ባሻገር ምጮች እንዲጎለብቱ ያደርጋል፤ የሚለውንም አርሶ አደሩ በተግባር እንዲገልጠው ማገዝ ይገባል።

ለምሳሌ፣ የተፋሰስ ልማት (የአካባቢ ጥበቃ ሥራ) መከናወኑ አርሶ አደሮቹ ከልቅ ግጦሽ የተጠበቁ የወል መሬዎች ላይ መኖ በማልማት፣ ከብቶቻቸውንም አስረው በመመገብ ብዙ ጥቅሞች እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በእርከንና መሰል የተፋሰስ ሥራዎችም ምርታማነትን ማሳደግ፣ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ በማልማት የገበያ ሰብሎችን በማምረት አመጋገባቸውን ማሻሻል እንዲችሉና ምርታማነትን እንዲያሳድጉ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ይሄን የሥራውን ቱሩፋቶች አርሷደሩ በላቀ መልኩ እንዲያጣጥማቸው እድል መፍጠር ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የወል መሬቶችን ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ እና ወጣቶችን በማደራጀት በመስጠት በአትክልትና ሌሎች ፍራፍሬ ልማት እንዲሠማሩ በማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ መሥራት ይገባል። ይህ ሲሆን ለተፋሰስ ልማት ሥራው በተጨማሪ አቅም ይሆናል። ምርታማነትን በማሳደግም አሁን ላይ እየናረ የመጣውን የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ለማረጋጋት ይጠቅማል።

በዚህ ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ የተፋሰስ ልማት ሥራው ያስገኛቸው ጠቀሜታዎች በግልጽ እየታዩ ሲሆን፤ በቀጣይነትም በጥናትና ምርምር የተደገፈ ሥራን ማከናወን ይጠይቃል። ምክንያቱም በተፋሰስ ልማት ሥራው የተከናወኑ በርካታ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ያስገኙት ውጤትና ጥቅም በአርሶ አደሩ ሕይወት ውስጥ የሚገለፁት፤ ተጠቃሚነቱንም የሚያረጋግጡት ከዚህ በሰፋ መልኩ ሲተገበር ነው።

በተፋሰስ ልማቱ በየዓመቱ በአርሶ አደሩ የሚሠሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የአካባቢ መራቆትን ከመከላከል፣ የአፈር ለምነትን ከመጠበቅና ምርታማነትን ከማሳደግ እንዲሁም የአፈር እርጥበት ከመቀነስ እና ውሃ መጠንን ከማሳደግ አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ በተለያየ መንገድ ከመስማትና ከማየት ባለፈ በተግባርም ጭምር እየተረጋገጠ ነው።

> የተፋሰስ ልማቱ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ከዚህ የሰፋና ከበርካታ ጉዳዮች ጋር ጭምር ሊያያዝ የሚችል እንደሆነ የዘርፉ ምሑራን የሚገልጹት ሐቅ ነው

የተፋሰስ ልማቱ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ከዚህ የሰፋና ከበርካታ ጉዳዮች ጋር ጭምር ሊያያዝ የሚችል እንደሆነ የዘርፉ ምሑራን የሚገልጹት ሐቅ ነው። ለአብነትም፣ የዓለም አቀፉን የአየር ንብረት መዛባት ተከትሎ ሀገራት እያጋጠማቸው ያለውን ያልተጠበቀ የአየር ንብረት መዛባት ሙሉ በሙሉ ማስቆም እንኳ ባይቻል ተፅዕኖውን መቀነስ ከብዙ ጠቀሜታዎቹ መካከል የሚጠቀስ ነው።

የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን በስፋት ተግባራዊ ማድረግ፣ በውሃ አካላት ላይ የሚደርስን በደለል የመሞላት እድል ይቀንሳል። ኢትዮጵያም በዚህ ረገድ የሠራችው ሥራ የተለያዩ ሐይቆችና ግድቦቿን በደለል ከመሞላት እየታደገላት እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ፣ የጎንደር የአፈር ምርምር ቤተ ሙከራ መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ወደ ጣና ሐይቅ ይገባ የነበረውን የአፈር ደለልና የጎጂ ንጥረ ነገር መጠን ከ50 በመቶ በላይ ቀንሶታል። ይህ የተረጋገጠውም ዩኒቨርሲቲው በተከታታይ ዓመታት ባካሄደው የምርምር ሥራ ነው።

በዚህ ጥናት እንደታየውም፤ በጎርፍ ታጥቦ ወደ ሐይቁ ይገባ የነበረውን «ፎስፈረስ» የተሰኘውን ጎጂ ንጥረ ነገር በግማሽ መቀነስ የተቻለ ችሏል። ይሄ ፎስፈረስ ደግሞ የሐይቁን ብዝኃ ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥልና የዓሣ ሃብቱን ጨምሮ ሌሎች በሐይቁ ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ዕፅዋትን በመጉዳት ዝርያቸው እንዲመናመን የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ባለፉት ዓመታት የተሠሩት የተፋሰስና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የሐይቁን ብዝኃ ሕይወት ከመሰል አደጋዎች መታደግ ማስቻሉን መረጃው ያሳያል።

ይህ ለአብነት ይጠቀስ እንጂ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ያሉ የግብርና እና ግብርና ነክ ተቋማትና ድርጅቶች የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው። ልማቱ ግቡን እንዲያሳካ በጥናት ተደግፎ ሊከናወን፤ የቅንጅት ሥራንም የሚጠይቅ በመሆኑ የሚመለከታቸው ተቋማትና ድርጅቶች በስፋት ሊሠሩበት ያስፈልጋል።

የተፈጥሮ ሃብት ልማት ሥራው የአካባቢ መራቆትን ከመከላከል፣ የአፈር ለምነትን ከመጠበቅና ምርታማነትን ከማሳደግ በተጨማሪ የብዝኃ ሕይወትን ሕልውና ጠብቆ በማቆየት ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር ነው። በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች አሁን ላይ በስፋት ተግባራዊ በመሆን ላይ በሚገኘው የተፋሰስ ልማት፤ በተከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ከእርሻ ማሳዎችና ከተዳፋት መሬቶች በጎርፍ አማካኝነት በከፍተኛ መጠን ይባክን የነበረውን አፈርና ውሃ ማስቀረት መቻሉን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የተፋሰስ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ጎን ለጎን፤ የተስተካከለ ከባቢያዊ ሥነ ምሕዳር ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም በአንድ በኩል በሀገራችን የተፋሰስ ልማቱ ውጤታማ እንዲሆን አርሶ አደሩን በማንቃት የተፋሰስ ልማቱ ያስገኛቸው ጥቅሞች ጎልተው እንዲታዩ ማድረግ ይገባል። በሌላ በኩል፣ የአፈር ለምነትንና እርጥበትን በማሳደግ የግብርና ምርታማነትንና የመሬቱን የዕፅዋት ሽፋንን ማሳደግ የቀጣይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ይገባል።

# ዜጎች ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መቆም አለባቸው

**ታሪኩ ዘለቀ**

የአንድ ሀገር ብሄራዊ ጥቅም በዋናነት በራሱ ሀብትና አቅም ላይ የተመሰረተ፤ በራሱ ይሁንታና ቁጥጥር ላይ የተመሰረተ ነው። ሀገር የተፈጥሮም ይሁን የሰው ሀብቷን ተጠቅማ የማደግ መብቷ የማይሸራረፍ የሉዐላዊነት መገለጫም ነው። ከሀገር ሲያልፍ ከውጭ ሀገራት ጋር በሚኖር ግንኙነትም ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የተለመደ ነው።

ሁሉም ሀገራት ‹‹ብሔራዊ ጥቅሜ›› በሚል የሚይዙትና የሚታገሉለት አጀንዳ አላቸው። ሀያላን ሀገራት ብሔራዊ ጥቅሜ የሚሉት እና ይሄንኑ ማዕከል አድርገው ከሌላው ዓለም ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት አላቸው። በተለይ የአደጉ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅሜን አስከብራለሁ ብለው ከተሳካ በዲፕሎማሲ መንገድ፤ አለፍ ካለም በኃይል ጭና ተጠቅመው በበርካታ ሀገራት የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲተጉ መመልከት የተለመደ ሆኗል። ዜጎቻቸውም የየሀገሮቻቸውን አጀንዳ በመደገፍ በጋራ ሲቆሙ ተመልክተናል።

ኢትዮጵያውያንም የሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሁሉ በጋራ ተዋድቀው በጋራ ሞተዋል። ኢትዮጵያ ለሉዐላዊነቷ እና ለብሔራዊ ጥቅሞቿ ያደረገቻቸው ጥሪዎች ሁሉ በመልካም ምላሽ የተቃኙ ናቸው። ለዚህ ከታላቁ የአድዋ ድል እስከ ሕዳሴው ግድቡ የተመዘገቡትን ሁነቶች መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያውያን ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ተቋማት በተሻገሩ አጀንዳዎች ብዙ የልዩነት ሀሳቦች ቢኖሩንም፤ ሀገርን ስለሚያፀኑ ጉዳዮች በትብብር መቆም ግን ዛሬም የትውልዱ የቤት ስራ ነው።

ሁሉም እቅዶች የሚሳኩት፣ ሁሉም ሀሳቦች የሚሟሉት፣ ሁሉም ተስፋዎች የሚኖሩት ሀገር ሲኖር ነው። ለዚህም ነው ዜጎች የሀገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ግድ ይላቸዋል የሚባለው። በእርግጥ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ጥቅም በአንድነት እና በፅናት መጠበቅ የሚችሉ ሕዝቦች መሆናቸውን የትናንት ታሪክና የቅርብ ጊዜ ሁኔታ ሁነኛ ማሳያም ናቸው። የሀገርን ልዕልና ማስጠበቅ ከትውልድ ትውልድ ከመንግስት መንግስት ሲሸጋገር የመጣ የኢትዮጵያ መለያ ባህሪ ነው።

ይሁን እንጂ አሁን ላይ በጥቂቶች ሀገር እና የአስተዳደር ሥርዓትን (ቢሮክራሲን) ያለመለየት ችግር፣ እንዲሁም ለግል ጥቅማቸው ባደሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ሲንፀባረቅ ይታያል። ይህ የጥቂቶች የተዛባ እይታ ደግሞ እያደገ ሲሄድ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዳ ተግባር ነው። ሊታወቅ የሚገባው ሥርዓትና መንግስታት በአንድ ሀገር ውስጥ ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ። ሀገር ግን ሕያው ሆና ትቀጥላለች። በመሆኑም ለማትለወጠው ሀገር ለጉዳዮቿ ዜጎች በአንድነት መቆም ካልቻሉ ደግሞ የሀገር ብሔራዊ ጥቅም ይጎዳል።

ከዚህ አኳያ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም ለድርድር ባለማቅረብ የሰላምና ዴሞክራሲ ግንባታን ማጠናከር የኢትዮጵያ የሕልውና ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ፤ ለዚህም አወንታዊ ድርሻን ማበርከት ደግሞ ከልሂቃንና ከፖለቲከኞች የሚጠበቅ፤ ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ተግባር መሆን አለበት። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምን አስጠብቆ ለማስቀጠል ሀገር እያጋጠማት ያለውን ፈተና በጋራ ለማለፍ ከመስራት ጎንለጎን፤ ሲቃወሙም ሀገርንና መንግስትን መለየት አስፈላጊ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአንድ ወቅት ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ሲሰጡ፣ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ በምታደርገው ጥረት ግለሰቦችና ቡድኖች በሀገራዊ ጉዳይ ላይ በአንድነት ከመቆም ይልቅ በተቃራኒ ጎን መታየታቸው ሀገሪቱ ወደ ግጭትና ጦርነት እንድትገባ አድርጓታል"፤ ብለው ነበር።

ይሄም ንግግር የሚያሳየው ደግሞ ግለሰቦች አልጣም ጥቂቶች በቡድን ተሰባስበውም ያሉ ከመንግስት ጋር ቅራኔ አለን ብለው ካሰቡ ተቃውሟቸውን በሁሉም መንገድ የማድረግ አካሄድ አሁን አሁን ላይ እየተለመደ መምጣቱን ነው። ብሔራዊ ጥቅምን በተመለከተ መለያየት፣ ጫፍና ጫፍ መሳሳብ ኢትዮጵያ ላይ ያልተለመደ ነው። ምክንያቱም ቀደም ባለው ጊዜ ኢትዮጵያ ከሌላ ሀገር ጋር በምታደርገው ጦርነት ኢትዮጵያውያን ራሳቸው የጀመሩትን የውስጥ ግጭት እንኳን ቢኖር ለጊዜው ቅራኔውን ትተው የውጭውን ጠላት እስኪያወድሙ ድረስ አንድ ይሆኑ ነበር። ይህ በአድዋ የታየ ነው።

በሀገር ላይ በርካታ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የኑሮ ውድነት፣ የሰላም እጦት፣ መፈናቀል፣ግጭት ቢኖሩም፤ እነዚህን ችግሮች ብቻ እየመዘዝን ከሄድን ብዙ የሚያስኮርፉ ነገሮች አሉ። ነገር ግን በማን ነው የሚኮረፈው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን በሀገር እንደማይኮረፍ በአግባቡ ሊገባን ይገባል

የአድዋ ጦርነት ሊጀመር ትንሽ ቀን ሲቀረው ጭምር ከጣሊያን ጎን የነበሩ ኢትዮጵያውያን፣ በኋላ ላይ የሀገራቸውን ህልውና ለማስጠበቅ የተመለሱና የሰሩ ነበሩ። እንዲህ ማድረጋቸው ጦርነቱን ለማሸነፍ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህ ደግሞ የሁል ጊዜ ኢትዮጵያውያን የሀገር ወዳድነት የውስጥ ስሜት ነው። በታላቁ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ተቃዋሚ ሳይኖር ሁሉም በጋራ ተስማምቶ የመደገፉም ምስጢር ይሄው ከውስጥ የሚመነጨው የሀገር ወዳድነት መንፈስ ነው።

አሁን ግን አዲስ ልምምድ እየታየ ነው። በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ እዛና እዚህ የሚቆሙ ግለሰቦችን ማየት ተለምዷል። እንዲህ ማድረግም እንግዳ ያልሆነ ነገር እየሆነ ነው። ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያለውንና ብሔራዊ ጥቅሟን ሊያስከብር የሚችለውን የባህር በር ለማግኘት የምታደርገውን እንቅስቃሴ የራሷ ዜጎች ሆነው የሚቃወሙ ቡድኖችንና ግለሰቦችን እየተመለከትን መሆናችንም የዚህ አብነት ነው።

ይህ አካሄድ ተገቢ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ነው። ምክንያቱም፣ የሀገራችንን የወደብ ጥያቄ እንዳይሳካ አሸባሪው አልሸባብ እንኳ ከሱማሊያ መንግስት ጋር ባይስማማም ለሶማሊያ ጉዳይ በሚል በአንድነት ቆሟል። በአንጻሩ ግን የኢትዮጵያን መንግስት የተቃወሙ መስሏቸውም ይሁን አውቀው ከሀገር ጥቅም ተቃርነው የቆሙ ጥቂት ግለሰቦች ታይተዋል። ነገር ግን በብሔራዊ ጥቅም ላይ ይሄን መሰል አቋም ሊኖር አይገባውም። በዚህ መልኩ በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ጉዳይ ላይ በተቃርኖ መቆም ደግሞ ነውርም ነው፤ ኢትዮጵያዊ ባህልም አይደለም።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢሆኑ እንኳን በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ቢለያዩም በተለይ በብሔራዊ አጀንዳዎች ላይ በጋራ ሊቆሙ ይገባል። እየሆነ ያለውም ይሄው ነው። የሀገርን ጥቅም በሚያስከብሩ ጉዳዮች ላይ፣ የሀገርን ኢኮኖሚ በሚያሳድጉ ጉዳዮች ላይ፣ የሀገርን ደህንነት በሚያስጠብቁ ጉዳዮች ላይ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የፖለቲካ አንቂዎች ሁሉም ዜጋ በጋራ መቆም ይገባዋል። ከዚህ በተቃራኒው ግን በሀገር ጥቅም ላይ ተቃርኖ መቆም ሀገርን አሳልፎ እንደመስጠት ይሆናል። መሰረታዊ በሆኑ በሀገራዊ እሳቤ እና በሀገረ መንግስት ግንባታ ላይ መቀራረብና መተባበር ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሀገር ካለ ብቻ ነው ሁሉም ነገር ሊኖር የሚችለው።

ታሪክ እንደሚመሰክረውም፣ ኢትዮጵያውያን በታሪክ አጋጣሚ በጋራ በቆሙባቸው ሀገራዊ ጉዳዮች ሁሉ አሸናፊ ናቸው። ይሄ የሸናፊነት ልዕልና ደግሞ እንደ መንግስትም፣ እንደ ተቋምም የሚወርዱ የሀገርን ጥቅምና ፍላጎት የሚያስጠብቁ አጀንዳና ጉዳዮችን የእኔ ብሎ ከመቀበል፤ ለአጀንዳና ጉዳዩ መሳካትም ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት ጋር የሚተሳሰርም ነው።

በእርግጥ የትኛውም የሀገርን ጥቅም የሚያረጋግጥ አጀንዳ የሚወለደው ከመንግስት፣ ከፓርቲዎች፣ ከቡድኖች፣ ሲያልፍም ከግለሰብ ሊሆን ይችላል። ለአጀንዳው ተፈፃሚነት መስራት ግን የብዙሀኑን ትብብር ይሻል። አጀንዳውን የእኔ ብሎ ለመቀበልና ለመተግበር ታዲያ ጥያቄው መሆን ያለበት፤ የአጀንዳው ግብ የሀገርንና የህዝብን ብሄራዊ ጥቅም ያረጋግጣል ወይ? የሚል መሆን አለበት።

ለምሳሌ፣ እንደ ሀገር አሁን እየታሰቡ ያሉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህ በገዢው መንግስት የሚመጡ ቢሆኑም፤ የሀገርን ጥቅም የሚያስከብሩ እስከሆኑ ድረስ መፈፀም እንዳለባቸው ሁሉም በአንድ ድምፅ ማመን አለበት። እንደዚህ አይነት የጋራ የሆኑ አጀንዳዎችን መያዝና የወል ትርክቶችን መፍጠሪያ አውዶችን መገንባት ከሁሉም ይጠበቃል። መንግስትም አቃፊ ሆኖ የጋራ ትርክት እንዲኖር ከሁሉ የበለጠ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ የሚቀርቡ አጀንዳዎች የህዝቡን ስነ ልቡና፣ ሞራልና እሴት ያገናዘቡ ዘላቂ አብሮነትንም የሚያፀኑ መሆንም አለባቸው።

የትኛውም የበለፀገ ሀገር መነሻው ድህነት የወለደው የሰላም እጦትና ችግር ነው። ሆኖም የትኛውም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ቢኖር፣ በሀገር ተስፋ መቁረጥ ግን ከቶውንም አይቻልም። በሀገር ላይ በርካታ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የኑሮ ውድነት፣ የሰላም እጦት፣ መፈናቀል፣ግጭት ቢኖሩም፤ እነዚህን ችግሮች ብቻ እየመዘዝን ከሄድን ብዙ የሚያስኮርፉ ነገሮች አሉ። ነገር ግን በማን ነው የሚኮረፈው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን በሀገር እንደማይኮረፍ በአግባቡ ሊገባን ይገባል።

ችግሮችን እየነቀሱ አኩራፊ ከመሆን ይልቅም፣ ችግሮቹ እንዲፈቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆንና መፍትሄ አማራጮችን ማቅረብ ከሁሉም የሚጠበቅ ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በታሪክ አጋጣሚ እንዳደረገቻቸው የነፃነት ትግሎች ሁሉ፤ አሁንም የተደራረበባትን የችግር ድሪቶ ገፍፎ ለመጣል የተለያዩ አጀንዳዎችን ቀርፃ እየሰራች ነው። እነዚህ አጀንዳዎች ከግብ እንዲደርሱ ደግሞ፣ የሂደቱ ፈተና የሆኑ ጉዳዮችን የማጥራት ስራ ያስፈልጋል።

የተለያየ አጀንዳ እና ፍላጎት ያላቸው አካላት/መንግስትም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ሌሎች አደረጃጀቶች/ነገሮችን የሚረዱበትና የሚተረጉሙበት፣ እንዲሁም የሚተነትኑበት መንገድ የተለያየ ነው። ይሄው የአረዳድ ልዩነት የሚፈጥርባቸውን ስሜትም ወደ ኅብረተሰቡ የሚያሰርጹት በየራሳቸው መንገድ ነው። ይሁን እንጂ ይሄን ሲያደርጉ ቢያንስ በሚያቀራረብና ወደ ሚያስማማው ለመምጣት እንዲችሉ በማድረግ ሊሆን ያስፈልጋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ የዴሞክራሲ ተቋማት እንደምርጫ ቦርድ፣ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የፌዴራል ኦዲተር የመሳሰሉ ተቋማት በተቻለ መጠን ገለልተኛ ሆነው እኩል የሚዳኙ፣ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ታማኝነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ይሄን ታማኝነት ሲያገኙ በመንግስትና ሕዝብ መካከል ትምምነት ስለሚፈጥሩ እንዲተገበሩና እንዲኖሩ በሚታሰቡ ብሔራዊ አጀንዳዎች ላይ ሁሉም ኃይሎች በጋራ የሚተባበሩበት አውድ ይፈጠራል።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ አሁን የጀመረችውን የባህር በር የማግኘት ጉዞን ጨምሮ ሌሎች የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም የሚያረጋግጡ ጥያቄዎች በውጤት ለመደምደም፤ በተለይ መንግስት ችግሮችን በሆደ ሰፊነት የመሻገር ልምምዱን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ በጋራ አለመቆም እና የሀገርን ገፅታ ለግል ጥቅም ለማዋል ሲባል ሆንብሎ ማበላሸት በሕግ ተጠያቂ ከማድረጉም ባሻገር የታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ተግባር መሆኑንም መገንዘብ ይገባል።

በመሆኑም በሀገራችን ጉዳይ ላይ የምንሰጠው አስተያየትና በመንግስት ላይ የምንሰጠው አስተያየት ለየቅል መሆን አለባቸው። መንግስትን መተቸት፣ መውቀስ፣ ማመስገን ይቻላል። ነገር ግን ሀገርን ማሳነስ፣ ሀገርን ተዳፍሮ ለጠላት መረጃ መስጠት፣ የሀገርን ገፅታ ጥላሸት እየቀቡ እንጀራ መብያ ማድረግ ታሪክም ሕዝብም ህግም ይቅር የማይላቸው ወንጀሎች ናቸው።

ምክንያቱም ሀገር ከሁሉ ነገር ትበልጣለች። መንግስታት የሚቀያየሩት በቋሚዋ ሀገር ውስጥ ነው። በመሆኑም ማንኛውም ዜጋ የሚኖረው እይታ ሁሉ ከዚህች ቋሚ ሀገር ጋር ሊሆን ይገባል። ስለ ኢትዮጵያ ስናስብ የቀደሙት ስለ እርሷ ራሳቸውን እንዴት አሳልፈው እንደሰጡ እናስብ፤ ገናን ታሪክና ዝናዋ፣ ስልጣኔና ጥበቧ ከምን የመነጨ እንደሆነ እናስላስል። ይሄን ማድረግ ስንችል በታላላቅ ሰዎች የዘለቀችውን የታላቋን ሀገር ጥቅም ለማስጠበቅ በጋራ በመሆም አቅም እናገኛለን።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# የኤሌክትሮኒክ ዘርፉን መምራት የሚያስችል ስትራቴጂ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

‹‹ዘመነ ዲጅታላይዜሽን›› ዓለም በየዕለቱ አዳዲስ ክስተቶችን እንድታስተናግድና በፍጥነት እንድትጓዝ እያደረጋት ይገኛል። ዛሬም ጥቅም ላይ ውለው አገልግሎት እየሰጡ ያሉት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ብዙ ሳይቆዩ በሌላ በተሻለ ቴክኖሎጂ በፍጥነት እየተተኩ ናቸው። በዚህ በኩል የዓለም አገራት በእኩል ደረጃ ለመወዳደር ባይችሉም፣ ወደ ሁዋላ የቀሩት የቀደሙት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉትን ሩጫ በእጅጉ የፈጠነ እንዲሆን እያደረገው ነው። በቴክኖሎጂው ወደኋላ የቀሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት በዘመነ ቴክኖሎጂ በመዋጀት የፈጠነውን ዓለም ይቀላቀሉ ዘንድ የመወዳደሪያ ምህዳሮችን መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያም የዲጂታል ዓለምን ለመቀላቀል የሚያስችላትን ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን በማድረግ ረገድ በርካታ ተግባራት እያከናወነች ትገኛለች። ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ተቀርጾ ዲጂታላይዜሽን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሥራዎችም እየተሰሩ ናቸው። ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የማድረጉን ሥራም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በበላይነት እየመራው ይገኛል። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ዲጂታላይዜሽንን በማስፋፋት ረገድ ዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጎ በርካታ ሥራዎች መስራት ተችሏል። በዚህም ከ526 በላይ የሆኑ የመንግሥት አገልግሎቶች በኤሌክትሮኒክ መንገድ እንዲፈጸሙ፤ የክፍያ ሥርዓቶችም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓት እንዲሆኑ እና የተለያዩ መተግበሪያዎች እንዲለሙ ተደርገዋል።

በዲጂታል ቴክኖሎጂው በኩል የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ሊያሰፉ የሚችሉ ሥራዎችን መስራት ተችሏል። ባለፈው ወር መጨረሻም የዲጂታል ሳምንት በማካሄድ በዲጅታል ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎችን ኅብረተሰቡ እንዲረዳቸውና እንዲገነዘባቸው ማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መስራታቸው ተመላክቷል።

ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ከተሰሩ ሥራዎች የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ አንዱ ነው። ስትራቴጂው በቀጣይ አምስት ዓመት የኤሌክትሮኒክ ዘርፉ የሚመራበትን አቅጣጫ ለማመላከት ታልሞ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ስትራቴጂውን አጠናቅቆ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የመጨረሻ ግብዓት ማሰባሰብ ተችሏል።

ስትራቴጂው በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል ሲሆን፤ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የመተግበሪያ ልማት፣ የሰው ኃይል ልማት፣ አወቃቀር እና በጀትን አካትቶ የያዘ መሆኑ ተገልጿል። ስትራቴጂው ከ2016 እስከ 2020 ዓ.ም ተግባራዊ ላይ የሚውል መሆኑም ተመላክቷል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶክተር) የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ የኢትዮጵያን የዲጂታል ሽግግር ለማፋጠን እንደሚያስችል ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ስትራቴጂው ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ለማሳካት እና የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ስትራቴጂው የመንግሥትን አገልግሎት በዲጂታል የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች ባሉበት ሆነው የመንግሥትን አገልግሎቶች በቀላሉ እንዲያገኙ እንደሚያስችል ሚኒስትሩ ተናግረዋል። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የመንግሥት አገልግሎቶች ቢያንስ 50 በመቶ ዲጂታል ማድረግ፣ ዲጂታል መታወቂያን በመጠቀም የኦንላይን አገልግሎቶችን በ25 በመቶ ለማሳደግ እና 50 በመቶ የመንግሥት አገልግሎቶችን ወደ ክላውድ ለማዛወር እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂ ቴክኒካል ሥራዎች አስተባባሪ ሊሻን አዳም (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ስትራቴጂው ከተለያዩ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ አማካሪዎች ጋር ከተጀመረ አንድ ዓመት ማስቆጠሩን ይናገራሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ የመጀመሪያው የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂ በ2002 ዓ.ም የተሰራ ሲሆን፤ ሁለተኛውም በ2007 ዓ.ም ተሰርቷል። ይህ ስትራቴጂም የቀደሙትን በመሞርከዝ የተሰራ ሲሆን፤ ለአምስት ዓመታት የተሰሩ ስትራቴጂዎችን በጥልቀት በመመልከት ወደፊት አሻግሮ ለማየት የሚያስችል ነው።

ስትራቴጂው ቀደም ካሉት ስትራቴጂዎች አንጻር ሲታይ ሰፋ ተደርጎ የተሰራ እና በቀጣይ አምስት ዓመታት አገሪቱ የምትመራበት መሆኑን ጠቁመዋል። አሁን ላይ ስትራቴጂውን ከክልሎች፣ ከመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ ከግል ዘርፉ ለተወከሉ እና ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ የመጨረሻ ግብዓት ለመሰብሰብ መቻሉንም ያመላክታሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከዚህ ቀደም የተሰሩ ስትራቴጂዎችና የመንግሥት እቅዶችን፣ (የአሥር ዓመቱን መሪ እቅድ፣ ዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ፣ አምስት ዓመቱን አገር በቀል የኢኮኖሚ እቅድ እና ሀገሪቷ የምትመራባቸው እቅዶች በመመልከት የተሰራ ነው። አሁን ላይ ከታችኛው ቀበሌ ጀምሮ እስከ ላይኛው አካል ድረስ ያሉ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን እርስ በርሳቸው በማገናኘትና መረጃ በማለዋወጥ ለኅብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ትስስር ለመፍጠር ይጠቅማል።

‹‹ስትራቴጂው ሲሰራ የመንግሥት እቅዶችን፣ በየእያንዳንዱ መስሪያ ቤት እና በክልሎች ያለውን የቴክኖሎጂ አፈጻጸም በተመለከተ ጥናት በማድረግ፣ የዓለም አገራት ተሞክሮ እና የአገልግሎት ተጠቃሚውን ማኅበረሰብ መረጃ በመሰብሰብ ስትራቴጂውን ለመንደፍ ተሞክሯል›› ይላሉ። ከዚህ በፊት ለሚመለከታቸው አካላት የቀረበና ግብዓት የተሰበሰበት መሆኑን ገልጸው፤ አሁን ለማጠቃለል የሚያስችል ግብዓት መገኘቱን ይናገራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ስትራቴጂው በአራት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል። የመጀመሪያው መተግበሪያ (አፕሌኬሽን) ነው፤ አሁን ላይ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አንድ አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቀሙት መተግበሪያ እንደየዘርፉ ይለያያል። እያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት የየራሱን መተግበሪያ በመስራት እየተጠቀመ ነው። ስትራቴጂው እነዚህን በምን መልኩ እርስ በርስ ማስተሳሰር ይቻላል? በሚቀጥሉት ጊዜያት እንዴት መቀጠል ይገባል? የሚለውን ማመላከት ያስችላል።

መተግበሪያዎች ስታንዳርድ ወጥቶላቸው በስታንዳርዱ መሰረት እንዲሰሩ ያስችላል። መንግሥት ለመተግበሪያ የሚያወጣውንም ወጪ በእጅጉ ይቀንሳል። ምክንያቱም ሁሉም መስሪያ ቤቶች የተለያዩ መተግበሪያዎች በሚያበለጽጉበት ጊዜ ብዙ ያስወጣል። መተግበሪያዎችን እየተጋሩ የሚሰሩ ከሆነ ግን የግድ በስታንዳርድ መመራት ስለሚጠበቅባቸው ወጪ ያስቀራል ሲሉ አብራርተዋል።

ስትራቴጂው ሁለተኛ ትኩረት ያደረገበት ጉዳይ ደግሞ መሠረተ ልማት ነው። መሠረተ ልማት በመዘርጋት የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን በኔትወርክ ማገናኘት ነው። ለአብነት አሁን ያለው ወረዳ ኔት የሚባለው ወረዳዎችን ከፌዴራልና ከክልል መንግሥት ጋር የሚያገናኝ መሰረተ ልማት ነው። ሌላኛው ደግሞ መረጃዎች የሚቀመጡበት ቋት (ዳታ ሴንተር) የመሳሰሉ ለመገንባት ምን መስራት አለበት የሚለውን በሰፊው የሚያሳይ ነው። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት መንግሥት በገነባቸው ዳታ ሴንተሮችም ይሁን በወረዳ ኔት መስራት የሚገባቸውን ሥራዎች ያመላክታል።

ሦስተኛው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉት ነገሮች (ኢንኤብለር) እና በቀጣይ መንግሥት ለኅብረተሰቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ምን ማድረግ አለበት? የሚለውን ይመለከታል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀየሩ ፖሊሲዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ መሻሻል ያለባቸው የሕግ ማዕቀፎች ሊኖሩ ይችላሉ። የመንግሥት መስሪያ ቤት ሠራተኞች በቴክኖሎጂ የተሻለ እውቀት እና የአሰራር ልምድ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው። በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) እንዴት ማሻሻል ይቻላል የሚለውን የሚዳስስ ነው። ምክንያቱም በተደረገው ጥናት እንደሚያመላክተው ብዙዎቹ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ከተመረቁ በኋላ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ወደፊት ሲሄዱ አይስተዋልም።

ይህም ወደፊት ለመጓዝ የሚያስችል እወቀት እንዲኖራቸው፣ ማበረታቻ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ ምን መስራት ያስፈልጋል የሚለው ለማየት ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪም የግሉን ዘርፍ ከመንግሥት የቴክኖሎጂ ማደግ አቅም ጋር እንዴት አጣጥሞ ማስቀጠል ይቻላል? የግሉ ዘርፍ በምን መልኩ ሊሳተፍ ይችላል? እንዴት ማበረታታት ይቻላል? ለሚሉት ሀሳቦች ምላሽ የሚሰጥም ይሆናል።

ተመሳሳይ የትምህርት ተቋማት መንግሥት በቴክኖሎጂ የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ በኩል እንዴት

> **የኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂ ለቀጣይ አምስት ዓመታት የሚያገለግል ነው። ስለዳታ፣ መተግበሪያ /አፕሊኬሽን ልማት/ እና በአጠቃላይ ዲጅታላይዜሽንን በተመለከተ አሁን የት ነን፤ በቀጣይ የት መድረስ አለብን፤ በዚህ ሂደትስ ምን መስራት ያስፈልጋል የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስም ያስችላል**

መርዳት እንደሚችሉ፣ ጥናቶችን በማካሄድም ሆነ ስርአተ ትምህርቱን በማሻሻል ተማሪዎች ዘመኑ የሚጠይቀውን የቴክኖሎጂ እውቀት እንዲላበሱ በማድረግ በኩልም ብዙ ሥራዎች እንደሚጠበቅባቸው ይጠቁማሉ። አሁን ላይ ያሉት ጥናቶች የሚያሳዩት ቴክኖሎጂ በጣም እያደገ የመጣ ቢሆንም፣ ስርአተ ትምህርቱ ግን ከዚህ እኩል መሄድ እንዳልቻለ ያመለክታሉ።

አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የተካተቱበት ነው። ከእነዚህም መካከል ዋንኛው ገንዘብ ነው። ኮምፒዩተር ለመግዛት፣ ዳታ ማዕከላትን ለማሻሻል፣ የሰው ኃይል ለማሰልጠን፣ የግሉን ዘርፍ ለማበረታታና መሰል ሥራዎች ለመስራት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ለማግኘት የሚቻልባቸውን መንገዶች ይጠቁማል።

ከዚህ በተጨማሪም በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ እያደገ የመጣው የቀጣናዊ ትስስር አገራትን እርስ በርስ የሚያገናኝ ነው። በተለይ የአፍሪካ ሀገሮች በብዙ መልኩ እርስ በርስ የሚገናኙ ናቸው፤ ወደፊትም ትስስሩ በጣም እየሰፋ ሊመጣ ይችላል፤ ይህን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሰራ ነው።

‹‹ስትራቴጂው ዓለም በዲጂታል ቴክኖሎጂው እየደረሰችበት ያለውን በመመልከት በሁሉም ዘርፍ ወደፊት ለማየት እንዲቻል ተደርጎ የተቀረጸ ነው›› የሚሉት አስተባባሪው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ለማድረግ የሚያስችልና ዲጅታል ኢትዮጵያን የበለጠ የሚያስፋፋ መሆኑን ይገልጻሉ። ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ እየተከለሰ መሆኑንም ጠቅሰው፤ ይህንን አካቶ የያዘ እንደሆነም አመላክተዋል።

ዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ የሰው ኃይል ስልጠና፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ትስስር፣ ወጣቶች በቴክኖሎጂ የሥራ እድል እንዲፈጥሩ እና መሰል ሥራዎችን ያካተተ መሆኑንም አንስተዋል። ይህ ስትራቴጂ በዲጅታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ ትኩረት ከተደረገባቸው በአንድ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመጨመር ዲጂታል ኢትዮጵያ አንዱ ክፍል የሆነው የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂ ለማዳበር በስፋት ለማየት የሚያስችል መሆኑንን ያመላክታሉ።

ስትራቴጂ በቀረበባቸው መድረኮች ጥሩ የሚባሉ አስተያየቶችና ግብዓቶችን መሰብሰብ መቻሉን የቴክኒክ አስተባባሪው የሚገልጹት። በቀጣይ ስትራቴጂውን በማጠናቀቅ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ እንደሚያስረክቡና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ እንደሚሆን ተናግረዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የብሔራዊ ኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ ማስተባባሪያ ዴስክ ኃላፊ አቶ ብሩህተስፋ ታዬ በበኩላቸው፤ የኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂ ለቀጣይ አምስት ዓመታት የሚያገለግል መሆኑን ይናገራሉ። ስትራቴጂው ስለዳታ፣ መተግበሪያ/አፕሊኬሽን ልማት/ እና በአጠቃላይ ዲጅታላይዜሽን በተመለከተ አሁን የት ነን፤ በቀጣይ የት መድረስ አለብን፤ በዚህ ሂደትስ ምን መስራት ያስፈልጋል የሚሉት ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ነው ይላሉ።

አሁን ላይ ጥናቱን ለማጠናቀቅና ስትራቴጂውን ወደ ተግባራ ለማስገባት የመጨረሻውን ግብዓት መሰብሰብ የተቻለ መሆኑ ይገልጻሉ። የስትራቴጂው ዓላማ በአገሪቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰሩ የዲጂታል ሥራዎች ከየት ተነስተው ወዴት መድረስ እንዳለባቸው ለማሳየትና ለመጠቀም ያለመ ነው። በጥናቱ ቀደም ሲል የተሰሩት ሥራዎች፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮዎችንና ተጠቃሚውን ኅብረተሰብ አስተያየት ለማካተት ተችሏል። በእነዚህ ጉዳዮች መነሻነት በአገሪቱ በቀጣይ አምስት ዓመታት በዲጅታላይዜሽን የሚሰሩ ሥራዎችን አካትቶ የያዘ ነው።

አቶ ብሩህተስፋ ቀደም ሲል እ.ኤ.አ በ2010 እና በ2015 የተሰሩ ሁለት ስትራቴጂዎች እንደነበሩ አስታውሰው፤ እነዚህ ስትራቴጂዎች የተሰሩባቸው ዓላማዎች እንዳሉ ሆነው በተለያዩ ምክንያቶች ብዙ ሥራዎች ሳይሰራባቸው የቀሩበትና እምብዛም ውጤታማ ያልሆኑ መሆናቸው ይናገራሉ። ይህ ሦስተኛው ስትራቴጂ ግን፤ የበፊቶቹ ጥናቶች ውጤታማ ያልሆኑባቸውን ምክንያቶች በማጥናት ወደፊትም መደረግ ያለበትን አካትቶ የተዘጋጀ መሆኑን አመላክተዋል።

የመንግሥት ኤሌክትሮኒክ ስትራቴጂና የኢንተር ፕራይዝ አርክቴክት ሰነድ በአንድ ላይ የሚዘጋጅ መሆኑን ገልጸው፣ ይህ ስትራቴጂ ተግባራዊ ሲደረግ የሚሰሩ ሥራዎች በጥናት ላይ የተሞረኮዙና ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚጓዙ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑን አቶ ብሩህተስፋ አስታውቀዋል፤ መንግሥት እንደ አንድ ተቋም ሆኖ በቅንጅት የሚመራበት መንገድን የሚያመቻች እንደሆነ ይገልጻሉ። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ክልሎችና ተጠሪ ተቋማት ተቀናጅተው የሚሰሩበት ስለሚሆን ሁሉም እንደ አንድ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ለአብነት አንድ ህንጻ አርክቴክቸር ተሰርቶ ሁሉንም በአንድ በማምጣት እንደ አንድ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

ስትራቴጂው ለዜጎችና ለተጠቃሚዎች፣ ለንግድ ተቋማት እና መንግሥታዊ ላልሆኑ እና ለመሰል ተቋማት አገልግሎትን በተቀናጀ፣ ወጪን በሚቆጥብና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚሰጥበትን መንገድ ያመቻቻል።

በስትራቴጂው የመጨረሻ ማጠናቀቂያ ወርክሾፕ ጥሩ ግብዓቶች መገኘታቸውን ጠቅሰው፣ ይህም ስትራቴጂውን የማዘጋጀቱን ስራ በፍጥነት ለማጠቃለል እንደሚያስችል ተናግረዋል። ስትራቴጂው ተግባራዊ ሲደረግ በቀጣይ ጊዜያት በአገሪቱ በዲጂታል ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች ውጤት የሚያመጡ እንዲሆኑ ያስችላል ሲሉ ሀሳባቸውን አጠቃለዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የኑሮ ውድነት መንስኤዎቹና መፍትሄዎቹ

**ክብረአብ በላቸው**

የኑሮ ወድነቱ ከወር እስከ ወር ከዓመት እስከ ዓመት በየጊዜው ማሻቀቡና ተባብሶ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በየጊዜው የሚያወጣቸው መረጃዎችና በማኅበረሰቡ ላይ የሚታየው የኑሮ ጫና ያመላክታል። በየጊዜው እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ወድነት አሁን ላይ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል በእጅጉ እየፈተነ ይገኛል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የኑሮ ወድነት ተከሠተ የሚባለው የማኅበረሰቡ የመግዛት አቅም ወይም ገቢ ማነስ ከዋጋ ግሽበት ጋር ተደምሮ የሚፈጥረው የመግዛት አቅም ሲዳከም ነው። በኢትዮጵያ ከመሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች እስከ ሌሎች ቁሳቁሶች ድረስ የዋጋ ግሽበቱ በየጊዜው እያሻቀበ ቢሆንም፣ የአብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ገቢ ወይም የመግዛት አቅም ግን ከዋጋ ግሽበቱ እኩል ማደግ አለመቻሉን የዘርፉ ባለሙያዎቸ ይገልጻሉ።

ለዋጋ ግሽበት ዋነኛ ምክንያቶች ከሚባሉት መካከል የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የገበያ ምኅዳር ብልሽት ወይም ሕገ ወጥ ደላሎች በገበያ ውስጥ የሚፈጥሩት ጣልቃ ገብነት እና የጥሬ ገንዘብ ሥርጭት መብዛት በቀዳሚነት የሚነሱ መሆናቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ እየታየ ላለው የዋጋ ግሽበት ዋና ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው የምግብ ነክ ሸቀጦች፣ በተለይ የእህል ዋጋ መናር ነው።

ሌላው የኑሮ ውድነት አባባሽ ምክንያት ከማሳ እስከ ገበታ ያለው የግብይት ሰንሰለት እጅግ የተራዘመ እንደሆነ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ምርት ከአምራቹ ወጥቶ ወደ ሸማቹ እጅ እስኪደርስ ባለው ሂደት በሚፈጠሩ ህገወጥ አሰራሮች ምክንያት በየደረጃው የዋጋ ጭማሪ ይስተዋላል፤ ይህም የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር ምክንያት ይሆናል።

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የኢኮኖሚ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ እንደሚናገሩት፤ የንግድ ሰንሰለቱ በተራዘመ ቁጥር ተዋንያኑ ብዙ ስለሚሆኑ ምርት በተፈለገው ጊዜ ወደ ተፈለገው ቦታ መድረስ አይችልም፤ ይህ ደግሞ የገበያ ቀውስ ይፈጥራል፣ ፈላጊው የፈለገውን ምርት በአይነት በመጠንና በጥራት እንዳያገኝ ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ሸቀጦች ከዋጋቸው በላይ ለገበያ እንዲቀርቡ ያደርጋል።

ይህ አካሄድ አቅርቦት ይቀንሳል፣ የምርት ፍሰት ያስተጓጉላል እንዲሁም የተሻለ ገበያ ይገኛል በሚል የምርት መከማቸት እንዲኖር በማድረግ በሚፈለገው ጊዜና ወቅት ለተጠቃሚው እንዳይደርስ ይሆናል። በተጨማሪ የምርት ጥራቱን ጭምር እንዲቀንስ ያደርጋል፤ በሌላ ጎኑ በሁሉም እርከን ላይ የአገልግሎት ክፍያ እየጨመረ ስለሚሄድ ምርት የመጨረሻ ተጠቃሚው ላይ ሲደርስ በጣም ውድ እንዲሆን ያደርጋል ይላሉ ምሁሩ።

አምራቹ ጋር ያለው ዋጋና የመጨረሻ ተጠቃሚው ኅብረተሰብ የሚገዛበት ዋጋ ስንመለከት ከግማሽ በመቶ በላይ ከፍ ያለ ዋጋ ነው ያለው የሚሉት ዶክተር ሞላ፤ ይህ የሚሆነው በደላሎች መብዛት እና እነርሱ ያልተገባ ጥቅም ለመግኘት በሚያደርጉት እሽቅድድም በመሆኑ ለዚህ መፍትሔ ማበጀት አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ።

ይህንን ችግር ለመፍታት በተለያየ ጊዜ መንግሥት የሚጀምረቸው ሥራዎች ነበሩ የሚሉት ባለሙያው ለአብነት እንደ ምርት ገበያ ባሉ ተቋማት እንደ ቡና፣ ስንዴ ቦሎቄ አይነት ምርቶች ገብተው ግብይት እየተካሄዱባቸው ነው። በተለይ ቡና ላይ የነበረው መንዛዛት የቡና ንግድ ሰንሰለት አስቸጋሪ ነበር። አሁን ያ ሰንሰለት ታልፎ በቀጥታ ሻጭና ገዥ እንዲገናኙ የሚያደርግ ስርዓት ነው የተዘረጋው። እንደዚህ አይነት አሰራሮች በሌሎች ምርቶች ላይም ተግባራዊ እንዲሆኑ በፕሮጀክት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በመደበኛ ሁኔታ ተግባር ላይ እንዲውሉ መንግሥት እስትራቴጂ ነድፎ ሥራ መሥራት አለበት ይላሉ።

ከአምራች ኢንዱስትሪ ወይም አርሶአደሩ ጋር የምርት ችግር የለም የሚል ዜና በተደጋጋሚ እንሰማለን የሚሉት ዶክተር ሞላ፤ ሆኖም የተመረተው ምርት በቀጥታ ሸማቹ ጋር ስለማይደርስ የዋጋ ንረት ይታያል። በተለይም መሃል ላይ ምርቱን አፍኖ የሚይዝ አካል ስለሚኖር በቂ ምርት ቢመረትም ሸማቹ ጋር የሚደርሰው ግን ጥቂቱ ነው። ስለዚህም በእነዚህ ችግሮች ላይ ጠበቅ ያለ ክትትልና እርምጃ መውሰድ ካልተቻለ ችግሩ የሚቀጥል መሆኑን ይናገራሉ።

ማንም ሰው ምርት ላይ እሴት ሰይጫምር ገብቶ የሚዳክርበት ሁኔታ መኖር የለበትም የሚሉት ምሁሩ ሁሉም እንደፈለገው የሚዳክርበት የንግድ ስርዓት የንግድ ስርዓቱን ጤናማ እንደማያደርገውና አልፎ ተርፎም ለኑሮ ውድነት መንስኤ እንደሚሆን አስረድተዋል። ስለዚህ መንግሥት ጊዜያዊ ሳይሆን በደንብ በፖሊሲና እስትራቴጂ የተደገፈ ማን ምን ማድረግ አለበት ከማን ምን ይጠበቃል የሚለውን በመለየት ወደ ሥራ በመግባት ችግሩ በዘላቂነት የሚቀረፍበት መንገድ ማበጀት አለበት ይላሉ።

በሀገሪቱ በአንዳንድ ቦታዎች የሚስተዋሉ ግጭቶች በማምራት ደረጃም፣ ምርት በመሰብሰብ ደረጃ እና የተመረተው ምርት ወደ ገበያ እንዳይቀርብ በማድረግ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል የሚሉት ዶክተር ሞላ፤ ግጭቶች የሚወገዱበትን መንገድ መተለም እንደሚገባ ጠቁመዋል። « ይህ እንዳለ ሆኖ የምርት ሰንሰለቱን የሚያራዝሙ አካለት በአስፈፃሚው እራሱ የሚታወቁ አይመስለኝም፤ ሰው ሰራሽ ግሽበት የሚፈጥሩ አካለት ሕገወጥ በሆነ መልኩ የተደራጁ ናቸው ይህንን መሰረታዊ በሆነ መልኩ መፍታት ይጠበቃል» ይላሉ።

ዶክተር ሞላ እንደሚሉት አርሶአደሩ ምርት ቤቱ ላይ እንዲቀመጥ የሚፈልግበት ምንም አይነት ምክንያት የለም። ቤቱ በቆየ ቁጥር ከጥቅም ውጭ ይሆናል እንጂ የሚሰጠው ፋይዳ አይኖርም። ስለዚህ አርሶአደሩ ያመረተውን ምርት ተጠቃሚው ጋር የሚያደርሱትና መሃል ላይ አንቀው በሚይዙት ደላሎች ነው። በጥራትም፣ በአይነትም፣ በብዛትም፣ በዋጋም እየተጎዳ ያለው የመጨረሻ ተጠቃሚው እንደመሆኑ ደህንነቱን ለማስጠበቅ የሀገሪቱን የንግድ ስርዓት የሚመሩ አካላት ተቋማዊ የሆነ አሰራር መከተል እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ዶክተር ሞላ እንደሚያስረዱት፤ የችግሩን አሳሳቢነት ሁሉም ሊረዳው ይገባል፤ አሁን ያለው የኑሮ ውድነት የህዝቡን አቅም እየተፈታተነ ነው ያለው፤ ይህ ደግሞ በተደጋጋሚ እንዳነሳነው ከተራዘመ የግብይት ስርዓት የመጣ ችግር ነው። ይህ ባይሆን በአንድና በሁለት ዓመት ልዩነት የምግብ እህል ዋጋ በአማካይ ከመቶ ፐርሰንት በላይ አድጎ የሚገኝበት ምክንያት ሊኖር አይችልም።

የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮችን ብቻ ሳይሆን የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ሀገር የምንስበው ስርዓት ያለውና የተቀላጠፈ የግብይት ስርዓት ሲኖረን ነው። ይህንን ለማድረግ ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህንን ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት ተገቢ በሆነ መልኩ መረባረብ አለባቸው ብለዋል።

በዚህ ጉዳይ አስተያየታቸውን የሰጡን ሌላኛው የኢኮኖሚ ባለሙያ ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ ናቸው። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ምርት ቀጥታ ከአምራቹ ወደ ተጠቃሚው የሚደርስበት ሁኔታ አለ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ከጅምላ አከፋፋይ ወደ ደንበኛ የሚደርስበት አጋጣሚ ይኖራል። በዚህ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ሰዎች እየገቡ ግብይቱን የሚያራዝሙበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህ የገበያ ሰንሰለት ላይ አንዳንዶቹ እሴት የሚጨምሩ ናቸው፤ በገበያ ሰንሰለቱ የሚሳተፍ አካል እሴት የሚጨምሩ ከሆነ ለኢኮኖሚው ጠቃሚ ነው ለአምራቹም በተዋረድ የሚሰጠው ጥቅም ይኖራል ይላሉ። ሆኖም ብዙዎቹ ምንም አይነት እሴት የማይጨምሩና አልፎ ተርፎም ለግሽበቱ ዋነኛ መንስኤ ሲሆኑ ይታያሉ።

ዶክተር ዳዊት ለአብነት ሲያነሱ፤ አንድ አምራች አዲስ አበባ ያለ ቢሆንና ተጠቃሚው ደግሞ ሀዋሳ ከተማ ነዋሪ ቢሆን ተጠቃሚው አንድ እቃ ገዝቶ ለመምጣት አዲስ አበባ ከተማ መሄድ አዋጭ አይሆንለትም። አንድ ነጋዴ ግን ተጠቃሚው ወዳለበት ከተማ ምርቱን ሲያቀርብ እሴት ጨምሯል ማለት ነው። በተቃራኒው ግን ምንም አይነት እሴት ሳይጨምር አንዱን ወደ ሌላው እየተቀባበለ ዋጋ ብቻ እየጨመረ የሚሄድበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ በፍጹም ተገቢነት የሌለው አካሄድ እንደሆነ ይናገራሉ።

ባለሙያው እንደሚናገሩት፤ እንደነዚህ አይነት ትክክለኛ ያልሆኑ አካሄዶች ናቸው የኑሮ ጫና ይዘው የሚመጡትና ጉዳት የሚያስከትሉት። ጉዳቱም የመጨረሻ ተጠቃሚ በሆነው ኅብረተሰብ ላይ እንደመሆኑ አየር በአየር የሚከናወኑ የንግድ ሥራዎች ከጠቀሜታቸው ይልቅ ጎጂነታቸው ስለሚበዛ እነዚህ አካሄዶች የማሳጠር ብሎም ሕገወጥ አሰራር የማስወገድ ሥራ መሠራት አለበት ይላሉ።

አምራች አካል ገበሬም ሆነ ፋብሪካ ያመረተው ምርት



ዶክተር ዳዊት ሀዬሶ



ሞላ ኃማርያም (ዶ/ር)

**የንግድ ሰንሰለቱ በተራዘመ ቁጥር ተዋንያኑ ብዙ ስለሚሆኑ ምርት በተፈለገው ጊዜ ወደ ተፈለገው ቦታ መድረስ አይችልም**

ለተጠቃሚው በተመጣጠኝ ዋጋ መድረሱን መረጋገጥ መቻል አለበት፤ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ከአምራቹ ይጠበቃል። በሌላ በኩል መንግሥት እንደ ተቆጣጣሪ አካል ይህ የተራዘመ የግብይት ስርዓት እንዲያጥር ከተቻለም ደግሞ እንዲጠፋ የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት ይናገራሉ።

ዶክተር ዳዊት አክለውም፤ በአሁኑ ወቅት በገበያ ስርዓቱ ውስጥ የሕገወጥ ደላሎች ሚና በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም በትክክል ይህን ያክል ነው ለማለት ጥናትን ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። እነርሱ የሚያገኙትን ጥቅም ብቻ ለማጉላት የምርት ዋጋ እንዲጨምር የማድረግ ሁኔታው በግልጽ የሚታይ ነው። ለምሳሌ የቤት ኪራይ ብንመለከት በብዙ የሀገሪቱ ከተሞች ላይ አከራይና ተከራይ የሚገናኙት በደላላ ነው። በዚህ ወቅት ከሁለቱም ወገን ገንዘብ የሚቀበሉ እንደመሆናቸው የሚያገኙትን ገንዘብ ከፍ ለማድረግ አነስተኛ ገቢ ባለው ተከራይ ላይ ጫና በመፍጠር የዋጋ ጭማሪ እንዲደረግ ይገፋፋሉ። ይህ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በደላሎች እጅ ላይ እየወደቀ መጥቷል የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው አካሄዱ በቶሎ መገታት ያለበት እንደሆነም ተናግረዋል።

እነዚህን ሕገወጥ አካሄዶች ሻጭና ገዢው በቀጥታ የሚገናኙበት መንገድ በማመቻቸት አነስተኛ ገቢ ያለው የማኅበረሰብ ክፍል በኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቂ ሆኖ እንዳይቀጥል ለማድረግ በዋናነት መንግሥት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት ሚናቸውን መወጣት እንደሚገባቸው ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር ዳዊት ገለፃ፤ የሸማቹን ጥቅም ለማስጠበቅና አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶችን ለማስወገድ የተለያዩ ሀገራት ማለትም ህንድ፣ ቻይናና ሌሎች የላቲን አሜሪካ ሀገራት በስፋት የሄዱበት መንገድ አለ። ያንን ልምድ መውሰድ ይቻላል፤ ይህም ልምድ ምንድነው፡- አንድን ምርት ማንም ያምርተው ለተጠቃሚው የሚደርሰው የመጨረሻ የመሸጫ ዋጋ ታውቆ ነው ወደ ገበያ የሚቀርበው። ያንን ምርት በምንም ተዓምር ከተተመነለት ዋጋ በላይ መሸጥ አይቻልም።

ተቆጣጣሪ ተቋማት የሻጩንም የገዢውንም መብት ማስጠበቅ ግዴታቸው ነው የሚሉት ባለሙያው፤ የተለያዩ ሀገራት ልምዶችን ከሀገሪቱ ነበራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ የግብይት ስርዓቱ የመጨረሻ ተጠቃሚው በማይጎዳበት ሁኔታ እንዲቀርብ ማስቻል እንደሚገባ ይገልፃሉ።

የተለያዩ ሀገራት ዜጎቻቸው ምርቶች በቅናሽ የሚገኙባቸውን መጋዘኖች ያዘጋጃሉ። ማንኛውም ዜጋ ከእነዚህ ተቋማት ሄዶ የፈለገውን የሚገዛበት አሰራር አላቸው፤ ኢትዮጵያም ከራሷ አቅም አንፃር በተለያዩ ከተሞች ዜጎች በቅናሽ የሚፈልጉትን ነገር የሚገበያዩበት እንደ የእሁድ ገበያ አይነት ያሉ አሰራሮች ጠንካራ መሠረት ኖሯቸው በቀጣይነት ቢተገበሩ የሚኖራቸው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ይናገራሉ።

ሌላው በኢትዮጵያ የሸማቾች ማኅበር ተብሎ ምርትን ከአምራች ተቋማት እየወሰደ ለተጠቃሚ በተመጣጠኝ ዋጋ ማድረስን ዓላማው አድርጎ የተቋቋመው ተቋም የተጠናከረ አለመሆንና ሸማች በሚፈልገው መጠን ምርት ከማቅረብ አንፃር ሰፊ ክፍተት ያለበት እንደመሆኑ ይህ ተቋም በተደራጀ መልኩ ሥራውን እንዲሰራ ማድረግ ሌላኛው አማራጭ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ዶክተር ዳዊት እንደሚናገሩት፤ በገዢው ኅብረተሰብ አካባቢ ያለው የመረጃ እጥረት ለኑሮ ውድነቱ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው። አንድ ምርት ከገበያ ሊጠፋ ነው ወይም ነገ አይኖርም ተብሎ አሉባልታ ሲነገር ተሻምቶ ያንን ምርት ለመግዛት የሚካሄድበት መንገድ ከመረጃ እጥረት የሚመነጭ በመሆኑ በሀገሪቱ የሚገኙ ሚዲያዎች ማኅበረሰቡ በቂ መረጃ እንዲኖረው ለማድረግ የራሳቸው ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ባለሙያዎቹ እንዳነሱት ጊዜ የማይሰጠውን የኑሮ ውድነት ችግር ለመፍታት ችግሮችን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መስራት ይገባል። በግብይት ሰንሰለቱ የሚስተዋሉ ማነቆዎች ምንድናቸው? በምን አይነት ሴክተር ላይ በብዛት ይታያሉ? መገለጫቸው ምንድነው? የሚለውን ጥናትን መሰረት አድርጎ መለየት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። <<ችግሩን በአግባቡ መለየት የመፍትሔው ሃምሳ በመቶ ድርሻ ይወስዳል>> እንደሚባለው የችግሩን መንስኤ በጥናት መለየት ያስፈልጋል፤ በመቀጠልም ችግሩ አንገብጋቢ እንደመሆኑ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አካላት በጉዳዩ ላይ ተቀጥሮ የተሰጣቸውን የራሳቸውን ሚና በተገቢው መልኩ መወጣት እንዳለባቸው ገልፀዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## የእንሰት ተክልን ለንፅህና መጠበቂያ

በስጥሻቸው ልዑልሰገድ





በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ችግሮችን የሚፈቱ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን ያበረከቱ ሴቶችን በተለያየ ጊዜ ተመልክተናል። በሀገራችንም በተለያዩ ጊዜያት የፈጠራ ስራ የሰሩ በርካታ ሴቶች አሉ። በዛሬው ጽሁፋችን በ2015 ዓ.ም የብሩህ ኢትዮጵያ የስራ እድል ፈጠራ ውድድር የተለየ የፈጠራ ስራ በማቅረብ ተሸላሚ የነበረችውና በጅማ ዩኒቨርሲቲ የማቴሪያል ኢንጂነሪንግ የትምህርት ክፍል መምህርት ከሆነችው ወይዘሮ ፋይዛ ሸምሱ ጋር ያደረግነውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል።

የተወለደችው በጉራጌ ዞን ቢሆንም ቤተሰቦቿ የመኖሪያ ቦታቸውን ቀይረው ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመምጣታቸው ከሁለት ዓመቷ ጀምሮ እድገቷ በአዲስ አበባ ከተማ ሆነ። ትምህርቷንም የተከታተለችው እዚሁ አዲስ አበባ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን አንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል በኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከሶስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ባሸዋም በመባል በሚጠራ ትምህርት ቤት፣ ከሰባተኛ እስከ ስምንተኛ ደግሞ ክፍል ፒያሳ በሚገኘው አፍሪካ አንድነት ትምህርት ቤት ተከታትላለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በራዲካል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ባሸዋም ትምህርት ቤት በማጠናቀቅ የመሰናዶ ትምህርቷን በአዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ተከታተለች። ፋይዛ በነበራት የትምህርት ቤት ቆይታ የደረጃ ተማሪ የነበረች ሲሆን ለኬሚስትሪ ትምህርት የተለየ ፍቅር ነበራት። ለኬሚስትሪ ትምህርት የነበራት ፍቅር አሁን ላለችበት ሙያም ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው ትናገራለች። የመሰናዶ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ወደ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ገባች። እዛም ከኬሚስትሪ ትምህርት ጋር የሚገናኝ የትምህርት ክፍል ስትፈልግ የማቴሪያል ኢንጂነሪንግ ቀልቧን ስለሳበው ምርጫዋ አደረገችው።

በወቅቱ የትምህርት ክፍሉ ገና አዲስ የተቋቋመ በመሆኑ ብዙ ተማሪ ለመምረጥ ይፈራ ነበር። ፋይዛ ግን ይህ የትምህርት ክፍል በውስጧ ከነበረው ፍላጎት ጋር ይቀራረብ ስለነበር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ምርጫዋ አደረገችው። በ2008 ዓ.ም በማቴሪያል ኢንጂነሪንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያዘች።

ፋይዛ ከምርቃት በኋላ ተከትሎ የሚመጣው የስራ ፍለጋ ውጣውረድ አላጋጠማትም 2008 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንደተመረቀች በጅማ ዩኒቨርሲቲ መምህርት ሆና ተቀጠረች። በ2009 ዓ.ም እዚያው ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን የመከታተል እድል ስላገኘች ስራ ሳትጀምር በቀጥታ ወደ ትምህርት ገባች። ሁለተኛ ዲግሪዋንም የተከታተለችው ማቴሪያል ኢንጂነሪንግ ነበር። ሁለተኛ ዲግሪዋንም እንደጨረሰች እዚያው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስራዋን ቀጥላ በመምህርነት ሙያ ላይ ተሰማርታ ትገኛለች።

ፋይዛ ከፍተኛ የምርምር ፍላጎት በውስጧ ስላለ በመምህርነት ሙያዋ እየሰራች የምርምር ስራዎችንም ታከናውናለች። የምርምር ውጤቶች መደርደሪያ ላይ ብቻ የሚቀሩ መሆን የለባቸውም የሚል አቋምም አላት። በወረቀት ላይ ተፅፈው ብቻ ከመቀመጥ አልፈው መሬት ላይ ወርደው ተግባራዊ የሚደረጉ ምርምሮችን የመስራት ከፍተኛ ፍላጎት ነበራት። የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሁፏን ጨምሮ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ምርምሮችን ሰርታለች።

የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ፅሁፏ ለግንባታ ስራ የሚያገለግል ጡብ (brick) ማምረት ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። የድንጋይ ከሰል ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ የሚወጣው አመድ ከሲሚንቶ ጋር ተመሳሳይ ባህሪ ያለው ነው የምትለው ፋይዛ፤ ይህ የድንጋይ ከሰል አመድ ያለ ጥቅም ተወግዶ አካባቢ ላይ ጉዳት ከሚያደርስ በድጋሚ ጥቅም ላይ ውሎ የሸክላ ጡብ ሊሰራበት ይችላል። ይህ ከድንጋይ ከሰል አመድ የሚሰራው የሸክላ ጡብ የመሰንጠቅ ሁኔታ ቢያጋጥመው እርጥበት በሚያገኝበት ወቅት ያለምንም ጥገና እርጥበቱን ብቻ በመጠቀም በራሱ ተመልሶ የመጠገን ባህሪ ያለው ነው ትላለች።

ጠንካራዋና አዳዲስ የምርምር ግኝቶችን ለመፍጠር ተኝታ የማታድረው ፋይዛ ታዲያ በተለያዩ የፈጠራ ስራ ውድድሮች ላይም ትሳተፋለች። በኢትዮጵያ በስራ እድል ፈጠራ ዘርፍና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚስተዋሉ ቁልፍ ተግዳሮችን ለመፍታት እና በአካባቢያቸው ያለውን ሃብት በመለየት አዳዲስ ሃሳቦችን ይዘው የሚመጡ ወጣቶችን ማበረታታትን ዓላማው አድርጎ ከሶስት ዓመት በፊት የተጀመረው የብሩህ ኢትዮጵያ የስራ እድል ፈጠራ ውድድርም ፋይዛ በ2015 ዓ.ም ተወዳድራ ሽልማት ያገኘችበት አንዱ ውድድር ነው።

በዚህ ውድድር ፋይዛ የምስክር ወረቀትን ጨምሮ 260 ሺህ ብር የገንዘብ ሽልማት ለማግኘት ችላለች። በውድድሩ ማሸነፏ እና የገንዘብ ሽልማት ማግኘቷ የሞራል መነሳሳት እንደፈጠረላት እና ወደፊትም በሌሎች የፈጠራ ስራዎች ላይም ጠንክራ መስራት እንዳለባት እንድታስብ ያደረጋት መሆኑን ትናገራለች። ከውድድሩ ባገኘችው የገንዘብ ሽልማትም የፈጠራ ስራዋን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚረዷትን ስራዎች ለመስራት እንቅስቃሴ ላይ መሆኗን ትናገራለች።

ይህንን ውድድር ለማሸነፍ ያበቃት፤ በፈረንጆቹ 2019 ኡጋንዳ ላይ በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ከአሜሪካ እንዲሁም ከኡጋንዳ ሴት ተማሪዎች ጋር በመሆን አፍሪካ ውስጥ ሴቶች በቀላሉ ሊሰሩት የሚችሉት የንፅህና መጠበቅያ እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን የሚል ሃሳብ በማመንጨት ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የቪዲዮ ምስሎች በስፋት ይወጡ ነበር።

በኋላ ግን ይህ በጋራ የተጀመረ ሃሳብ ፋይዛ ወደ ኢትዮጵያ በመመለሷ በጋራ የሚሰራ ሊሆን አልቻለም። ፋይዛ ታዲያ ወደ ሀገሯ ተመልሳም ሃሳቡን ከጭንቅላቷ አላወጣችውም ነበርና ከሃሳቡ ጋር የሚገናኙ የተለያዩ የዩቲዩብ ቪዲዮዎችን መመልከት ጀመረች።

የፋይዛ ወላጅ እናት ተወልደው ያደጉት በጉራጌ ዞን የገጠር አካባቢ ነው። የጉራጌ ዞን የምትታወቅበት የእንሰት ተክል ከምግብነቱ ባሻገር የጉራጌ ሴቶች ሲወልዱ ወይም የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት የእንሰት ቅርንጫፍ አድርቀው በማንጠፍ የሚተኙበት የንፅህና መጠበቂያ መሳሪያቸውም ጭምር ነው። የእንሰት ተክል ግንዱ ውሃ አያሳልፍም፤ የቅርንጫፉ ለስላሳ ክፍል ደግሞ ፈሳሽን አምቆ የመያዝ አቅም አለው።

ፋይዛ ይህንን የጉራጌ ሴቶች የእንሰት አጠቃቀም ከእናቷ በሰማች ጊዜ እጅጉን ተደነቀች፤ ነገሩ ቀልቧን ሳበው። የእንሰት ተክሉን እንድታመጣላት እናቷን ጠይቃ የተነገራትን መሞከር ፈለገች። በሙከራዋም ተክሉ ውሃ እንደማያሳልፍ ለማረጋገጥ ቻለች። ወዲያው ይህንን ነገር ወደ ምርምር መቀየር እንዳለባትና የእንሰት ተክልን በመጠቀም የንፅህና መጠበቂያ መስራት እንዳለባት አሰበች። በሃሳብ ብቻም አልቀረችም ባደረገችው ምርምር ከእንሰት ተክል የሴቶች የንፅህና መጠበቂያ መስራት ቻለች። ለውድድሩ አሸናፊነትም ያበቃት ይሄው የምርምር ስራ ነው።

ይህንን የምርምር ውጤት በምትሰራበት ወቅት የተለያዩ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን ለማየት ሞክራ እንደነበር የምትናገረው ፋይዛ፤ አብዛኞቹ ምርቶች ሙሉ ለሙሉ የተሰሩት ከፕላስቲክ እንደሆና እነዚህ ፕላስቲኮች የሚሰሩት ከነዳጅ በመሆኑ በጤና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው ትገልፃለች። ከዚህ ባሻገር እነዚህ ከፕላስቲክ የሚሰሩ የንፅህና መጠበቂያዎች በሙቀት ወቅት የማቃጠልና የማሳከክ ባህሪ እንዳላቸውም ታስረዳለች።

እነዚህ የንፅህና መጠበቂያ ምርቶች የሚመረቱበት ጥሬ እቃ ከውጪ የሚገባ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋጋው እጅግ እየጨመረ ሄዷል። አገልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላም ቶሎ የመበስበስ ባህሪ ስለሌላቸው አካባቢን የመበከል አቅማቸው ከፍተኛ ነው። ከእንሰት የሚሰሩት የንፅህና መጠበቂያዎች እንደሀገር ገበያ ላይ ቢውል የሚሰራው ከባዮማስ(biomass) እንደመሆኑ ለጤና ተስማሚ ከመሆኑ ባሻገር ዋጋውም እንደሌሎች የፅህና መጠበቂዎች ውድ አይሆንም፤ አገልግሎት ላይ ከዋለ በኋላም ቶሎ የመበስበስ ባህሪ ስላለው የአካባቢ ብክለትን ይቀንሳል ትላለች።

አዕምሮዋ ሁሌም ለአዲስ ነገር ዝግጁ የሆነው ፋይዛ ምርምሯን በእንሰት ተክል ብቻ አላበቃችም። አንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ ውሎ ከሚጣለው የንፅህና መጠበቂያ ባሻገር ለረጅም ጊዜ እየታጠበ አገልግሎት መስጠት የሚችል የሴቶች ንፅህና መጠበቂያም ለመስራት ችላለች። ይህንን ስራዋን የስፌት ማሽን በመግዛት ቤት ውስጥ በማምረት የጀመረች ሲሆን ምርቱን ያስተዋወቀችው በአዲስ አበባ ብቻ ነበር። ነገር ግን አዲስ አበባ ውስጥ የንፅህና መጠበቂያን አጥቦ የመጠቀም ልምድ እስከዚም በመሆኑ ተቀባይነት ማግኘት አልቻለችም። ክልሎች እና በተለያዩ የገጠር አካባቢዎች ለማሰራጨት ብታስብም አብሯት የሚሰራ ተቋምም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ተቋማት ባለማግኘቷ ምርቱን ለተጠቃሚ ማድረስ አልቻለችምና ለጊዜው ማምረቷን እንዳቆመች ትናገራለች።

‹‹ትልቁ ሃሳቤ ምርቴ ሰው ጋር ደርሶ ተጠቃሚ እንዲያገኝ ማድረግ ነው›› የምትለው ፋይዛ ምርቶቹን ለማምረት የሚረዱ የተለያዩ ማሽኖችን ማቅረብ የሚችል አካል ካለ አብራ ለመስራት ዝግጁ መሆኗን ትገልፃለች። በተጨማሪም ስራው ምርት የሚመረትበት ሰፊ ቦታ የሚያስፈልገው በመሆኑ ይህንን የሚያሟላልኝ አካል ቢኖር የፈጠራ ስራዬ በተግባር ተተርጉሞ ሰዎች ዘንድ መድረስ ይችላል ትላለች። ታጥበው በድጋሚ አገልግሎት ላይ መዋል የሚችሉ የንፅህና መጠበቂያዎች ተመርተው በእጇ ላይ የሚገኙ በመሆኑ እነዚህን ምርቶች ከበጎ አድራጎት ተቋማት ጋር በመሆን በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚገኙ ሴቶች ማሰራጨት እንደምትፈልግ ጨምራ ትናገራለች።

ፋይዛ የዩኒቨርሲቲ መምህርት እንደመሆኗ በርካታ ተማሪዎችን የእውቀት እናት በመሆን ታሳድጋለች። እሷ ካላት የፈጠራ ችሎታ በመነሳት ተማሪዎቿ የሚሰሯቸው የመመረቂያ የምርምር ስራዎች ወደ ተግባር የሚለወጡና በርካቶችን የሚጠቅሙ ሃሳቦች ላይ እንዲያተኩሩ ዘወትር ትመክራለች። በክፍል ውስጥ በምታስተምርበት ወቅትም ተማሪዎቿ በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን በተግባር ምን እንደሚመስል እንዲረዱ የተለያዩ ቪዲዮዎችን ይዛ በመግባት እንዲመለከቱ ታደርጋለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ አዳዲስ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ሴቶች ይበረታታሉ የምትለው ፋይዛ፤ እንዳጠቃላይ ግን ሴት ልጅ በተለይም ልጅ ካላት ደካማ ተደርጋ የመቆጠሩ ነገር አሁንም አለ። ነገር ግን ይህንን ጫና ተቋቁማ ነጥራ ከወጣች በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት እድል አላት ትላለች።

በመንግስት በኩል ሴቶችን እናበረታታለን የሚሉ ነገሮችን በተለያዩ ሚዲያዎች ሲነገር እንሰማለን፤ አሁንም ግን በፈጠራው ዘርፍ ሴቶችን በግንባር ቀደምትነት በመደገፍና በማበረታታት በኩል መንግስት ብዙ ሊሰራው የሚገባ ነገር እንዳለ ትናገራለች። በርካታ እድሉን ያላገኙ ነገር ግን እድሉን ቢያገኙ ሀገር መለወጥ የሚችል የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ሴቶች በየቤታቸው ተቀምጠዋል፤ ይህንን የሚለውጥ እድል ሊፈጠርላቸው ይገባል ትችላለች ፋይዛ።

ወደ መሬት ወርደው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ሃሳቦችን በማመንጨት በኩል ሴቶች የተሻለ ሀሳብ የማመንጨት ብቃት በተፈጥሮ ተሠጥቷቸዋል። ያሉባቸውን የተለያዩ ጫናዎች አሸንፈው ወደፊት መውጣትና ችሎታቸውን ማሳየት አለባቸው። እንደሀገር ያለንበት የኢኮኖሚም ሆነ የቴክኖሎጂ እድገት በብዙዎች ላይ የፈጠራ ስራቸውን ለማውጣትና ተግባራዊ አድርጎ ለማሳየት የሚያዳግት ቢሆንም ሴቶች በተቻላቸው አቅም ሁሉ በውስጣቸው የያዙትን እምቅ አቅም አውጥተው ማሳየትና ተግባር ላይ ማዋል አለባቸው ባይ ናት።

**በመንግስት በኩል ሴቶችን እናበረታታለን የሚሉ ነገሮችን በተለያዩ ሚዲያዎች ሲነገር እንሰማለን፤ አሁንም ግን በፈጠራው ዘርፍ ሴቶችን በግንባር ቀደምትነት በመደገፍና በማበረታታት በኩል መንግስት ብዙ ሊሰራው የሚገባ ነገር እንዳለ ትናገራለች**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**አንድ ሜትር ተኩል እርዝማኔ ያለው እባብ፤ ከሰው ልጅ ሆድ ውስጥ ይቅርና በናሽናል ጂኦግራፊ ላይ እንኳን አለ እንዴ? ሲያስብለንና ሲያስደንቀን ይችላል። ይህ ታዲያ እዚሁ ሀገራችን ውስጥ በጎጃም ብቸና፤ ከአንድ ግለሰብ ሆድ ውስጥ ሲላወስ ወጥቷል ይለናል የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ። በ1951 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ብዙ ጉዳዮቹ ግርምትን የሚያጭሩ ሆነው እናገኛቸዋለን። መሪዎች በአዲስ አበባ በስብሰባቸው አንበጣን ስለማጥፋት ሲመክሩ፤ የአንበጣ መንጋውም በተመሳሳይ ሰዓት ከበረሃ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ በማድረግ መውጫ መግቢያውን ወረው ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፤ የእንስሳቱ ዓለም ዳራ የደረሰበት ሌላ ሆኗል። የሐረርን ጅብ ምን ነካው?...ከሰው አፍ ሥጋን ተካፍሉ እንዳልበላ፤ አሁን አጥሩን ጥሶ በመግባት የታዳጊውን ጉንጭ ቦትርፎታል። "...ወስላቶቹ ተይዘዋል" እነዚህ ወስላቶች እነማን ናቸው? ሁሉም በዛሬው "አዲስ ዘመን ድሮ" ተሰናስነው እናገኛቸዋለን።**

**የአንበጣ መንጋ መጣ ሲንጋጋ**

ትላንት ከሰዓት በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ሲያንዣብብ የነበረው የአንበጣ መንጋ የመጣበት "ግልጽ የሆነ ጉዳይ" የተሳካለት አይመስልም። በረሃውን ለቆ እስከ አዲስ አበባ ድረስ የመጣበት ዋናው ጉዳይ በመናገሻ ከተማው ውስጥ የሚገኘውን የአንበጣ መከላከያ ዋና መሥሪያ ቤት ለመውረር ነበር።

የአዲስ አበባ ቤቶች ሁሉ ጣራቸው የተሸፈነው ተመሳሳይ በሆነ የሻገተ ቆርቆሮ ስለሆነ፤ መሥሪያ ቤቱን ለይቶ ሊያውቀው የቻለ አይመስልም።

አንበጣው ከመጣበት ጉዳዮች ሁለተኛው፤ በአፍሪካ አዳራሽ ስለ አንበጣ መከላከያ ይደረግ የነበረውን ጉባኤ ለመቃወም ይመስላል። ዳሩ ግን አንበጣው የደረሰው ጉባኤው ከተበተነ ስለሆነ፤ በጉዞው የተደሰተ አይመስልም።

በፍልውሀ አቅራቢያ በአስፋልቱ መንገድ ላይ አርፎ የነበረውን አንበጣ መኪና ሲፈጨው በአየር ላይ ደግሞ ያንዣብብ የነበረውን፤ የሰማይ አዕዋፍ እየተከታተሉ ይለቅሙት ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙት ሰው፤ መኪናና የባሕር ዛፍ ቅጠል ይዞ በመውጣቱ፤ አገር አቋርጦ የመጣው የአንበጣ ወራሪ የዕለት ምሳውን ሳያገኝ ግራና ቀኝ ተበታትኖ የቀረ ይመስላል።

"ደጅ ያልተከላከሉት ሌባ ከማጀት ይገባ" እንደሚባለው ሁሉ እነሆ አንበጣው እስከ ዋና መሥሪያ ቤቱ ድረስ መጥቷል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 3 ቀን 1951 ዓ.ም)**

**ልጁን ጅብ ነከሰው**

ሐረር፤ በ26/8/1951 ዓ.ም ለ27 አጥቢያ ከሌሊቱ በግምት 6 ሰዓት ሲሆን፤ ከኤረር አውራጃ ፖሊስ ጽ/ቤት በስተምዕራብ በግምት 2 ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኘው ዲምቱ ከተባለው ቀበሌ አመድ አብዱላ የተባለውን የኢሣ ፊር ጎሣ ዕድሜው 14 ዓመት የሆነውን ልጅ እበረት ውስጥ ከብቶች መሐል ተኝቶ ሳለ ጅብ አጥሩን ጥሶ ገብቶ በስተግራ ጉንጩ ላይ ነክሶት አንጎሉን በመፈጥፈጥ ከአጥሩ ውጭ ይዞት ሲሔድ በመከታተል በሁለት ጥይት ተኩስ ከጅቡ አፍ ያስጣሉት መሆኑን፤ በመግለጽ ወንድሙ የሆነው ቡህ አብድላ በ27/8/1951 ዓ.ም ከጠዋት በሁለት ሰዓት ላይ ቁስለኛውን በቃሬዛ ይዞ በመቅረብ ስለአመለከተ፤ በፖሊስ ክፍል አስፈላጊውን ሕክምና የተደረገለት መሆኑን የአዳልና ኢሣ አውራጃ ግዛት ፖሊስ ጽ/ቤት በአስተላለፈው ደብዳቤ አረጋግጧል።

**ከሰው ሆድ ውስጥ 1 ሜትር ተኩል እባብ ወጣ**

በጎጃም ጠቅላይ ግዛት በብቸና አውራጃ በይናጭ ም/ወረዳ ግዛት አራሾች ጊዮርጊስ ከተባለው አገር ውስጥ አበበ ዓለምነህ የተባለ ሰው ከ4 ዓመት ጀምሮ የሆድ ውስጥ ሕመም አድሮበት በሕክምናና በአገር ልምድ መድኃኒት ብዙ ዓመታት ሲያሳልፍ ቆይቶ ሳለ ፤ በያዝነው ወር በዚሁ አውራጃ ደብረ ወርቅ ከተባለው አገር ላይ ጠበል ሲጠጣና ሲጠመቅ ከሰነበተ በኋላ፤ በአራተኛ ቀኑ ቁጥራቸው የበዛ እንደ እንሽላሊት ወይም እንደ ዓሣ መልክ የሆኑ ነፍሳት በሠገራ ከወጡለት በኋላ፤ በመጨረሻ አንድ እባብ እስከነፍሱ ቁመቱ አንድ ሜትር ተኩል የሚሆን ስለወጣ ይህ ተዓምር በዚያው ለተሰበሰቡት በሽተኞች ታይቶ በበትር ተይዞ ከቤተ ክርስቲያን ቀርቦ በእግዚአብሔር ምሕረትና በጠበሉ ፈዋሽነት ነዋሪውና የአካባቢው ሕዝብ የተደነቀበት መሆኑን የብቸና አውራጃ ግዛት በቁጥር 2ሺ ሁለት መቶ 27 ጽፎ በላከው ማስረጃ ተረጋግጦአል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 7 ቀን 1951ዓ.ም)**

**በጫካ ይኖሩ የነበሩት ሦስቱ ወስላቶች ተይዘዋል**

የሠላማዊውን ሰው ነፍስ በማጥፋትና እንዲሁም ገንዘብ በመቀማት የሚኖሩት 1ኛ/እሸቴ ዓለሙ 2ኛ/ዘለቀ ባዩህ 3ኛ/ዘነበ አየለ የተባሉ ወስላቶች በአርማጭሆ ወረዳ በጋለገር ም/ወረዳ ግዛት ደዚ ቢሆን ከተባለው ቀበሌ በትውልድ ሀገራቸው ውስጥ የተጠቀሰውን ወንጀል በመፈጸም ሲኖሩ፤ የዚሁ ክፍለ አገር አጥቢያ ዳኛ አቶ ዘሪሁን ገብረየስና የሀገሩ የነጭ ለባሽ ሹማምንቶች እንዲሁም ሕዝቡም ሀሳባቸውን በመደገፍ ወስላቶቹ ሚያዚያ 27 ቀን 1951 ዓ.ም ከበረሃ የከብት እረኞችን ስንቅና እንዲሁም የተላላፊውን ሰው ልብስ እያስወለቁና ገንዘብም መቀማታቸውን ስለተሰማ፤ ወዲያውኑ ሕዝቡ ሁሉ ከተሰበሰበ በኋላ፤ ይገኛሉ ከተባለበት ቦታ ሌሊቱን በዙሪያው ከቦ አድሮ ሲነጋ እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠይቃቸው አንያዝም በማለት ከጉድባ ገብተው ስለተኮሱባቸው መልሰው እሩምታ በመተኮስ አንደኛውን ዘለቀ ባዩህ የተባለውን ወንጀለኛ አቁስለው ሲያዝ፤ እንዲሁም ዘነበ አየለ የተባለውን ሳይቆስል ሁለቱም ከነመሣሪያቸው ተይዘዋል። ሦስተኛው እሸቴ ዓለሙ የተባለው ስላመለጠ አሁንም በመታደን ላይ ሲሆን፤ የተያዙትን ወስላቶች የዚሁ ቀበሌ ሕዝብ በአጥቢያው ዳኛ አማካይነት ቁስለኛውን ተሸክመው ያልቆሰለውን በገመድ ጠፍረው አምጥተው፤ ግንቦት 5 ቀን 1951 ዓ.ም ለአውራጃው ገዥ ሰጥተዋል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 2ቀን 1951ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ የወሮበሎች ብጥብጥን ተከትሎ የኤምባሲ ሠራተኞቿን ከሄይቲ አስወጣች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ በወሮበላ ቡድኖች አመጽ እየታመሰች ካለችው ሄይቲ መሠረታዊ ያልሆኑ የኤምባሲ ሠራተኞችን ከሀገሪቱ በአየር ማስወጣቷን ገለጸች። አሜሪካ በሄይቲ ዋና ከተማ ፖርት-አው-ፕሪንስ በሚገኘው ሚሽኗ የፀጥታ ጥበቃንም አጠናክራለች።

በዚህ ሳምንት በአውሮፕላን ማረፊያ፣ በፖሊስ ጣቢያዎች እና በማረሚያ ቤቶች ላይ ጥቃት ያደረሱት ወሮበሎች የሄይቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ኤሪዬል ሄንሪ ከሥልጣን እንዲወርዱ ግፊት እያደረጉ ነው። ለሦስት ቀናት ተጥሎ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአንድ ወር ተራዝሟል።

"በዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ አካባቢ እና በአውሮፕላን ማረፊያው አቅራቢያ በተፈጠረው የወሮበሎች ጥቃት ምክንያት የስቴት ዲፓርትመንት ተጨማሪ የኤምባሲ ሠራተኞች ለቀው እንዲወጡ ወስኗል" ሲል ኤምባሲው በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ለጥፏል። ኤምባሲው ክፍት ሆኖ እንደሚቆይም አክሏል።

በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች የሄሊኮፕተር ድምፅ መስማታቸውን በመጥቀስ ከማለዳ በፊት የተደረገው ዘመቻ በሄሊኮፕተር የተካሄደ መሆኑን ኤኤፍፒ የዜና ወኪል ዘግቧል። እሁድ እለት በሄይቲ የጀርመን አምባሳደርም ከሌሎች የአውሮፓ ኅብረት ተወካዮች ጋር ወደ ዶሚኒካን ሪፐብሊክ መሄዳቸውን የጀርመን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዜና ወኪሉ ተናግሯል።

ባለፈው ሳምንት ጠቅላይ ሚኒስትር ሄንሪ ወደ ክልላዊ ስብሰባ ሲሄዱ ወሮበሎች ጥቃታቸውን አጠናክረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማክሰኞ ዕለት ወደ ፖርት-አው-ፕሪንስ ለመመለስ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቶ መዳረሻቸውን ለመቀየር ተገደዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ መዳረሻቸውን የቀየሩት ታጣቂዎች በዋና ከተማዋ የሚገኘውን ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ለመቆጣጠር መሞከራቸውን ተከትሎ አየር ማረፊያው በመዘጋቱ ነው።

ሄንሪ ኬንያን ከጎበኙ በኋላ ምንም አይነት የሕዝብ መግለጫ አልሰጡም። ሚኒስትሩ ከፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ጋር ተገናኝተው ምሥራቃዊ አፍሪካዊቷ ሀገር የሄይቲን ፀጥታ ወደ ነበረበት ለመመለስ የተደረሰውን ስምምነት ለማዳን ነው።

ሁለቱ መሪዎች 2ሺህ የኬንያ ፖሊሶች ወደ ሄይቲ እንዲላኩ መንገድ የሚከፍት ስምምነት ተፈራርመዋል። ነገር ግን አንድ የኬንያ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ ስምምነቱን ፍርድ ቤት ወስደውታል። በፖርት-አው-ፕሪንስ ውስጥ ያሉ ወሮበሎች የጠቅላይ ሚኒስትሩን አለመኖር በመጠቀም ተከታታይ የተቀናጀ ጥቃቶችን ፈጽመዋል።

ከእስር ቤቶችም በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞችን



አስመልጠዋል። ብጥብጡ የሄይቲ ሰብዓዊ ቀውስ የበለጠ እንዲባባስ አድርጓል። ወሮበሎቹ ሄንሪን ከሥልጣን ከማስወገድ ባለፈ ዓላማቸው ምን እንደሆነ አልተናገሩም።

ጂ9 የተባለውን የወንበዴ ቡድኖችን ጥምረት የሚመራው የቀድሞ የፖሊስ አባል ጂሚ ሼሪዝየር (ባርቤኪው)፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሄነሪ ከሥልጣን የማይወርዱ ከሆነ "የእርስ በርስ ጦርነት" እንደሚኖር ዝቷል።

ብጥብጡ 362 ሺህ የሄይቲ ዜጎችን ከቀያቸው ማፈናቀሉን የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) ተናግሯል። ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሕጻናት ናቸው። በሄይቲ የአይኦኤም ኃላፊ ፊሊፕ ብራንቻት በሰጡት መግለጫ "ሄይቲ ሰዎች ጥሩ ኑሮ መምራት አልቻሉም። በፍርሃት እየኖሩ ነው፣ እና በየሰዓቱ ይህ ሁኔታ እየቀጠለ ነው፣ ጉዳቱ እየባሰ ይሄዳል" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## በረራ ላይ ሳሉ የተኙ ሁለት የኢንዶኔዢያ አየር መንገድ አብራሪዎች ምርመራ ተከፈተባቸው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በኢንዶኔዢያ በረራ ላይ ሳሉ ለ28 ደቂቃዎች ተኝተው በነበሩ ዋና አብራሪ እና ምክትል አብራሪ ላይ ምርመራ መከፈቱ ተገለጸ። የሀገሪቱ የትራንስፖርት ሚኒስቴር የባቲክ አየር መንገድ አብራሪዎች ከሥራ ታግደው ምርመራው እየተካሄደባቸው እንደሆነ አስታውቋል።

ሁለቱ አብራሪዎች በረራ ላይ ሳሉ እንቅልፍ የጣላቸው ከ7 ሳምንታት በፊት በነበረ ወደ መዲናዋ ጃካርታ ሲደረግ በነበረ የሀገር ውስጥ በረራ ላይ ነበር። አብራሪዎቹ ምንም እንኳ ለበርካታ ደቂቃዎች ተኝተው የነበረ ቢሆንም 153 መንገደኞችን እና የበረራ ሠራተኞችን ጭኖ የነበረው ኤርባስ ኤ320 አውሮፕላን በመዳረሻው በሠላም አርፏል።

የሀገሪቱ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ባወጣው ሪፖርት ዋና አብራሪው እረፍት ማድረግ ስለሚፈልግ ምክትል አብራሪው በረራውን እንዲቆጣጠር ኃላፊነት ሰጥቶታል። የ28 ዓመቱ ምክትል አብራሪም ትዕዛዙን ተቀብሏል። ይሁን እንጂ ምክትል አብራሪውም ሳያውቀው እንቅልፍ ወስዶት ነበር። ይህን ተከትሎ በጃካርታ የሚገኙ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ሁለቱን አብራሪዎች በራዲዮ አማካኝነት ለማነጋገር ያደረጉት ጥረት ምላሽ ሳያገኝ ቆይቷል።

አሁን ላይ እየወጡ ያሉ ሪፖርቶች እንደሚሉት ከሆነ ሳያውቀው እንቅልፍ የጣለው ምክትል አብራሪ በቅርቡ መንታ ልጅ የተገላገለች ባለቤቱን በልጅ እንክብካቤ ሲረዳ ቆይቷል። አብራሪዎቹ ከእንቅልፍ እስኪነቁ ድረስ የሬዲዮ ግንኙነቱ ለ28 ደቂቃዎች ተቋርጦ ነበር። የትራንስፖርት ሚኒስቴር ባወጣው ሪፖርት ላይ ዋና አብራሪው ከእንቅልፉ ሲነቃ ምክትል አብራሪው እንደተኛ እና አውሮፕለኑ ከበረራ አቅጣጫው ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወጥቶ እንደነበረ ተገንዝቧል ይላል።

ከክስተቱ በኋላ ሁለቱ አብራሪዎች ለአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ክፍል ምላሽ በመስጠት አውሮፕላኑን በጃካርታ አሳርፈዋል። ከበረራ በፊት ለአብራሪዎቹ የተደረገ የጤና ምርመራ ለበረራ ብቁ መሆናቸውን አሳይቶ ነበር። ደም ግፊታቸው እና የልብ ምታቸው ችግር ያልታየበት ሲሆን አልኮል በሰውነታቸው እንደሌለም በምርመራ ተረጋግጧል።

ይሁን እንጂ የኢንዶኔዢያ የአየር ትራንስፖርት ኃላፊ ክሪስቲ ኤንዳህ ሙራኒ አየር መንገዱ ሠራተኞቹ በቂ እረፍት እያገኙ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት በማለት ለባቲክ አየር መንገድ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ አስተላልፈዋል።

አየር መንገዱ በበኩሉ ሠራተኞች በቂ እረፍት ማግኘት አለባቸው በሚል ፖሊሲ እንደሚመራ ገልጾ ወደፊት ተመሳሳይ ክስተቶች እንዳያጋጥሙ ምክረ ሃሳቦችን እንደሚቀበል አስታውቋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት

# ኢትዮጵያ - በ13ኛው መላ አፍሪካ ጨዋታዎች

ብርሃን ፈይሳ

የፓን አፍሪካን ማሳያ ከሆኑ ስፖርታዊ ውድድሮች መካከል አንዱና ዋነኛው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች እአአ በ1965 ለመጀመሪያ ጊዜ በኮንጎ አዘጋጅነት ነበር የተካሄደው። በኦሊምፒክ መርህና ስርዓት በየአራት ዓመቱ የሚከናወነው ይህ ውድድር፤ በአፍሪካ ሕብረት፣ በብሄራዊ የኦሊምፒክ ኮሚቴዎች እንዲሁም በአፍሪካ የስፖርት ኮንፌዴሬሽኖች በጋራ ይመራል። ከጊዜ ወደጊዜ እያደገና እየሰፋ በመምጣትም ለኦሊምፒክ እንደማጣሪያ ውድድር እስከመጥቀም የደረሰ ሚናም አለው።

ወራት ብቻ የቀሩትን የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክን ተከትሎም የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች በጋና አዘጋጅነት ለ13ኛ ጊዜ መካሄድ ከጀመረ ቀናቶች ተቆጥረዋል። ምዕራብ አፍሪካዊቷ ሃገር ውድድሩን በዋና ከተማዋ አክራ እና ሌሎች ከተሞቿ ኩማሲ እና ኬፕ ኮስት ያሰናዳች ሲሆን፤ ለዝግጅቱም 145 ሚሊየን ዶላር ወጪ በማድረግ የኦሊምፒክ ደረጃውን የጠበቀ ሁለገብ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን መገንባቷን አስታውቃለች። ለሶስት ሳምንታት በሚቆየው በዚህ ውድድር ላይም ከ54 የአፍሪካ ሃገራት የተወጣጡና በሺዎች የሚቆጠሩ አትሌቶች በ30 ዓይነት ስፖርታዊ ውድድሮች ለአሸናፊነት የሚፋለሙ ይሆናል። ይህም እአአ በ2019 ከተካሄደው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች በአራት ብልጫ ያለው ነው።

ከጥቂት ቀናት በፊት ውድድሩ በተጀመረበት ዕለት በተከናወነው የጠረጴዛ ቴኒስ ስፖርት ግብጽ በሁለቱም ጾታዎች ቀዳሚውን ሜዳሊያ በማስመዝገብ በደረጃ ሰንጠረዡ ቁንጮ የተቀመጠች ሃገር ልትሆን ትችላለች። በአንጻሩ በነጠላ እና በቡድን በተካሄደው በዚህ ውድድር ላይ ተሳታፊ የነበረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አልተሳካለትም። ከፍተኛ ፉክክር ሲያካሂድ የቆየው የሴቶች ብሄራዊ ቡድኑ ወደ ግማሽ ፍጻሜ ለማለፍ በሚያስችለው ጨዋታ በናይጄሪያ አቻው 3 ለ0 ተሸንፏል። የወንዶች ቡድኑ ደግሞ በመጀመሪያው ዙር ጨዋታ ከምድቡ ማለፍ አልቻለም።




በመላው አፍሪካ ጨዋታዎች የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች የሴቶች ቡድን ዛሬ ኡጋንዳን ይገጥማል፣

በእግር ኳስ ስፖርት 8 ቡድኖችን በሚያፋልመው የመላ አፍሪካ እግር ኳስ ውድድር ኢትዮጵያ በሴቶች ብሄራዊ ቡድኗ እንደምትወከል ይታወቃል። ቡድኑ ከ20 ዓመት በታች ዓለም ዋንጫ ማጣሪያ እስከመጨረሻው ምዕራፍ ቢደርስም ሳይሳካለት መቅረቱ የሚታወስ ነው። ይህንን ተከትሎም ካፍ በመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ እንዲሳተፉ ካደረጋቸው ቡድኖች መካከል አንዱ ሲሆን፤ በሁለት ምድብ ተከፍሎ በሚካሄደው ጨዋታ ተሳታፊ ነው።

የኢትዮጵያ ወጣት ብሄራዊ ቡድኑም በምድብ አንድ ከአስተናጋጇ ጋና፣ ኡጋንዳ እና ታንዛኒያ ጋር ተደልድሎ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ልምምዱን ሲያከናውን መቆየቱ ይታወሳል። የመጀመሪያ ጨዋታውን በኬፕኮስት ስታዲየም ከአዘጋጇ ሃገር ጋና ጋር በማድረግ አንድ ለምንም በሆነ ውጤት መሸነፉ የሚታወስ ነው። በአሰልጣኝ ዮሴፍ ገብረወልድ የሚመራው ብሔራዊ ቡድኑ ሁለተኛ ጨዋታውን ዛሬ የሚያደርግ ሲሆን፤ የኡጋንዳ አቻውን ይገጥማል። ቡድኑ ከሁለት ቀናት በኋላ ደግሞ ሶስተኛ የምድብ ጨዋታውን ከታንዛኒያ ጋር በኤልሚና ስታዲየም ያከናውናል።

ኢትዮጵያ በመላ አፍሪካ ጨዋታዎች የተካፈለችበት ሌላኛው ውድድር የውሃ ዋና ሲሆን፤ በሴቶች የ100 ሜትር የደረት ቀዘፋ ለግማሽ ፍጻሜ አልፋለች። በሁለቱም ጾታ 50 ሜትር የቢራ ቢሮ ቀዘፋ እና 100 ሜትር የደረት ቀዘፋ ውድድሮች የተደረጉ ቢሆንም፤ በውድድሩ ሃገሯን የወከለችው ዋናተኛ ብርሃን ደመቀ በማለፍ በብቸኝነት ፍጻሜው ላይ እንደምትካፈልም ታውቋል።

በመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ውድድር ከሚካሄድባቸው ስፖርቶች መካከል 7 የሚሆኑት የኦሊምፒክ ስፖርቶች ናቸው። ከእነዚህ መካከልም ኢትዮጵያ በአምስቱ ስፖርቶች (አትሌቲክስ፣ ብስክሌት፣ ውሃ ዋና፣ ጠረጴዛ እና ሜዳ ቴኒስ ስፖርቶች ውጤታማ ለመሆን አልማለች።

በአጠቃላይ 149 አትሌቶችን የሚያቅፈው ቡድኑ በአትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ቦክስ፣ ብስክሌት፣ ወርልድ ቴኳንዶ፣ ሜዳ ቴኒስ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ውሃ ዋና እና ቅርጫት ኳስ ስፖርቶች ትፎካከራለች።

በዚህ የውድድር መድረክ በርካታ ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ቀዳሚ የሆነችው ግብጽ ስትሆን፤ 1ሺ635 ሜዳሊያዎችን አስቆጥራለች። 1ሺ326 እና 1ሺ54 ሜዳሊያዎች ያሏቸው ናይጄሪያ እና ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ሁለተኛ እና ሶስተኛ በመሆን ሰሜን አፍሪካዊቷን ሃገር ይከተላሉ። 174 ሜዳሊያዎች ያሏት ኢትዮጵያ ደግሞ በደረጃ ሰንጠረዡ 7ኛ ደረጃ ላይ ስትገኝ፤ ከእነዚህ ውስጥ 45ቱ የወርቅ፣ 54ቱ የብር እንዲሁም 75ቱ የነሃስ ሜዳሊያዎቹ ናቸው።